በምርምር ጉዳዮች ም/ፕሬዝደንት ጽ/ቤት የ2009 ዓ.ም.

<u>የአራተኛው ሩብ አመት እና የአመቱ እቅድ ክንውን ሪፖርት</u>

## ክፍል አንድ፡ ገለጻ

### 1.1. መግቢያ

ሐረማያ ዩኒቨርስቲ በሀገሪቱ ውስጥ ካሉት ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት መካከል ቀደምትና አንጋፋ ከሆኑት አንዱ ሲሆን ከ65 በላይ ለሆኑ አመታት በተለያዩ የትምህርት ዘርፎች በከፍተኛ ደረጃ የሰለጠነ የሰው ኃይል በማፍራትና ሀገራዊ ጠቀሜታ ያስገኙ ዘርፈ-ብዙ የምርምር ውጤቶችን በማፍለቅ ሲሰራ ቆይቷል፡፡ የሐረማያ ዩኒቨርስቲ የምርምር ጉዳዮች ጽ/ቤት የዩኒቨርስቲዉን የምርምርና የምርምር ውጤቶች ስርጸትን በማስተባበርና በመከታተል ዩኒቨርስቲው በምርምር ስራና ውጤት የላቀ ደረጃ እንዲደርስ ከፍተኛ ጥረት በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡ በተለይም በግብርናው የምርምርና ስርጸት ዘርፍ ዩኒቨርስቲው ፊር ቀዳጅ ሲሆን በዘርፉም በርካታ ፊርጥ ተመራማሪዎችን ያፈራና በርካታ የምርምር ውጤቶችንና ቴክኖሎጂዎችን እና የፖሊሲ ሃሳቦችን በማፍለቅ፣ በማላመድና በማስራጨት የማህበረሰቡን ተጠቃሚነት ለማጎልበት የበኩሉን አስተዋጽኦ አበርክቷል፡፡ እስካሁን ባለው መረጃ መሰረት ዩኒቨርሲቲው ወደ 145 የሰብል ዝርያዎችንና ሌሎች በርካታ ቴክኖሎጂዎችን አመንጭቶ በጥቅም ላይ እንዲውሉ አድርጓል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ በርካታ የእንስሳት ዝርያዎችንና የእንስሳት መኖቴክኖሎጂዎችን በማዳቀልና በማላመድ ለአካባቢው ማህበረሰብ እንዲሰራጩና ከዚሁም ተጠቃሚ እንዲሆን አድርጓል፡፡ በተጨማሪም በርካታ ሳይንሳዊ የምርምር ውጤቶችን በዓለም-አቀፍ ድርሳናትና መጻህፍት መልክ አሳትሟል፡፡ ከ1980ዎቹ ጀምሮ ዩኒቨርሲቲው ከግብርና በተጨማሪ ሌሎች በርካታ የትምህርት መስኮች መከፈቱን ተከትሎ የምርምርና ስርጸት ዘርፉም ያደገ ሲሆን በአሁኑ ወቅት በ6 የምርምር ትኩረት መስኮችና በ23 ንዑስ ትኩረት መስኮች ስራውን እያካሄደ ይገኛል፡፡ የምርምር ጉዳዮች ም/ፕሬዝዳንት ጽ/ቤት የተጠቀሱትን የትኩረት መስኮች ለማሳካት በምርምር ቡድኖችና አጋርነት፣ በምርምር ስርጸትና ህትመት እና በምርምር ፋሲሊቲዎች ማኔጅመንት ዳይሬክቶሬቶች ተዋቅሮ እየሰራ ይገኛል፡፡ በዚሁ መሰረት በምርምር ቡድኖችና አጋርነት ስር ላሉት ስድስት የምርምር ትኩረት መስኮች ስድስት የምርምር ትኩረት መስክ መሪዎች በዳይሬክቶሬት ደረጃ እየሰሩ ይገኛሉ፡፡

የምርምር ቡድኖችና አጋርነት ዳይሬክቶሬት የምርምር ስራዎችን የማስተባበር፣ የመከታተል፣ ድጋፍ የመስጠት ስራና የዩኒቨርሲቲውን የምርምር ስራ ከሌሎች ባለድርሻ አካላትና የምርምር ሀገር አቀፍና አለም አቀፍ ድጋፍ አድራጊ ድርጅቶች ጋር የማስተሳሰር ስራዎችን እያከናወነ ይገኛል፡፡ የምርምር ስርጸትና ህትመት ዳይሬክቶሬት የምርምር ውጤቶችን፣ እውቀቶችን፣ ቴክኖሎጂዎችንና አዳዲስ አሰራሮችንና መልካም ተሞክሮዎችን ለተጠቃሚዎች እና ለባለድርሻ አካላት ያደርሳል እንዲሁም እንዲደርስ ያስተባብራል፡፡ በተጨማሪም ተመራማሪዎች የምርምር ግኝቶች በምርምር ድርሳናት፣ በመጻህፍት መልክ፣ በፕሮሲዲንግ እና በሌሎች የህትመት አይነቶች እንዲታተሙ የማበረታታት፣ የማሳተምና የማሰራጨት ስራዎችን እንዲሁም ስራዎቹን በብዙሃን መገናኛዎች እንዲተዋወቁ ያደርጋል፡፡ የምርምር ፋሲሊቲዎች ማኔጅመንት ዳይሬክቶሬት የምርምር ፋሲሊቲዎችን የማስተዳደር፣ የማስፋፋት፣ የማዘመን፣ በአግባቡና በፍትሃዊነት ስራ ላይ እንዲውሉ የማድረግ፣ የምርምር ግብዓቶችን የመለየት፣ የማቅረብ፣ የማከፋፈል፣ በተገቢው መንገድ ስራ ላይ መዋላቸውን የመከታተልና የማረጋገጥ ስራዎችን ያከናውናል፡፡

### 1.2. የሪፖርቱ ዓላማ፣ ሪፖርቱ የሚሸፍነዉ ጊዜ፣ አዘገጃጀትና አቀራረብ ስልት

ይህ ሪፓርት በምርምር ጉዳዮች ም/ፕሬዚዳንት ጽ/ቤት ስር በ2009 ዓ.ም. የአራተኛውን ሩብ አመት እና የአመቱን የስራ ክንውን ለማሳወቅ ታስቦ የተዘጋጀ ነው፡፡ ሪፓሪቱ የሚሸፍነው ጊዜ ከሐምሌ 1/ 2008 ዓ.ም. እስከ ሰኔ 30/ 2009 ዓ.ም. ነው፡፡ ይህ ሪፖርት በምርምር ጉዳዮች ም/ፕሬዚዳንት ጽ/ቤት ስር የሚገኙ የስራ ክፍሎችን ሪፖርት ያካተተ ነው፡፡

### 1.3. የምርምር ጉዳዮች ጽ/ቤት ተልዕኮ፣ ራዕይ፣ እሴትና የትኩረት አቅጣጫዎች

**ተልዕኮ**

ፍላጉት ተኮርና ጠቃሚ ምርምሮችን በተለያዩ መስኮች በማካሄድ የምርምር ቴክኖሎጂዎችን፣ እውቀቶችንና መልካም ተመክሮዎችን በማፍለቅ፣ በማስገባት፣ በማላመድ፣ በመለየትና በማሰራጨት የህብረተሰቡን ኑሮ ማሻሻልና ማሳደግ፡፡

**ራዕይ**

የሀረማያ ዩኒቨርሲቲ እ.ኤ.አ. በ2025 ከአፍሪካ በምርምር ተመራጭ ከሆኑ ዩኒቨርሲቲዎች ውስጥ አንዱ እንዲሆን ማስቻል፡፡

**እሴት**

1. **አካዳሚያዊ ነፃነት፡-** የመማር-ማስተማርና የምርምር ስራዎች በነጻነትና በዲሞክራሲያዊ መንገድ እንዲካሄዱ፣ ግለሰቦች ጥልቅ ምርምር ማድረግ እንዲችሉ፣ በመማር-ማስተማር፣ በምርምርና በልማት ስራዎች እንዲሳተፉ ለማስቻል ምቹ ሁኔታዎችን ለመፍጠር ዩኒቨርሲቲው በቁረጠኝነት ይሰራል፡፡
2. **ቁርጠኝነት፡-** የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ የተሰጣቸውን ስራና የተጣለባቸውን ሀላፊነት ዕውቀታቸው በፈቀደ ደረጃ በቁርጠኝነት፣ በተነሳሽነትና በታማኝነት ለመወጣት የሰራሉ፡፡
3. **መልካም አስተዳደር፡-** ዩኒቨርሲቲው ዲሞክራሲያዊ፣ ግልፅ፣ ሁሉን አሳታፊ፣ ሀላፊነትና ተጠያቂነት የተሞላበት አመራርን ያሰፍናል፣ የእኩል ተጠቃሚነት መርሆን ያራምዳል፡፡
4. **ልዩነትን ማክበር፡-** ዩኒቨርሲቲው እኩልነትና ፍትሀዊነት በሁሉም መልኩ እንዲሰፍንና ልዩነቶችን (በፆታ፣ በብሄር፣ በሀይማኖት፣ በዘር፣ በጎሳ፣ በእድሜ፣ በአካል ሁኔታ፣ ወዘተ) አክብሮ ይሰራል፡፡
5. **ሙያዊ አሰራርን መሰረት ማድረግ፡-** የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ ለላቀ ሁሉን ዓቀፍ ሙያዊ ስነምግባር ተገዥ ይሆናል፡፡
6. **በጋራ የመስራት ባህልን ማዳበር፡-** የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ እርስበርስና ከባለድርሻ አካላት ጋር በመግባባት በጋራ የመስራት ባህልን ያዳብራሉ፣ የእኛነትን መንፈስና ሃላፊነትን የመቀበል መርሆ ያሳድጋሉ፡፡
7. **የፈጠራ/ግኝት ክህሎትን ማዳበር፡-** የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ የስራ፣ የአዳዲስ ግኝቶችና ፈጠራዎች ባለቤት የመሆንና አቀናጅቶ የመተግበር ባህልን ያዳብራል፡፡
8. **ተፈጥሮና አካባቢን መንከባከብ፡-** ዩኒቨርሲቲው የተፈጥሮ ሀብትንና አከባቢን ለመጠበቅ፣ ለመንከባከብና፣ በአግባቡና ተፈጠሮን በማይጎዳ መልኩ ለመጠቀም በቁርጠኝነት ይሰራል፡፡

**መሪ ቃል**

ለልማት መሰረት እንጥላለን!

## ክፍል ሁለት፡ የዝግጅት ምዕራፍ ሥራዎች አፈጻጸም

- ከተለያዩ ኮሌጆች ለተውጣጡ መምህራን የንድፈ ሀሳብ አጻጻፍና የመረጃ ትንተና እንዲሁም የሪፖርት አቀራረብ ላይ ስልጠና ተሰጥቷል፡፡
- የምርምር ፋሲሊቲ አጠቃቀምና አቅርቦት ዙሪያ ዳሰሳ ተካሂዶ፣ በፍትሃዊነት እንዲዳረሱ ተደርጓል፡፡
- ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ለተውጣጡ ሞያተኞች የምርምርና ቴክኖሎጅ ሽግግር ክህሎት ስልጠና ተሰጥቷል፡፡
- በዩኒቨርሲቲው የገንዘብ ድጋፍ የሚካሄዱ የምርምር ስራዎች ተለይተዋል፡፡

## ክፍል ሦስት፡- የትግበራ ምዕራፍ ሥራዎች አፈጻጸም

### 3.1. የመልካም አስተዳደርና የለዉጥ ሥራዎች አፈጻጸም

መልካም አስተዳደርን ለማስፈን የምርምር ጉዳዮች ም/ፕሬዝዳንት ጽ/ቤት በየደረጃው ቅሬታዎችን እያስተናገደ መፍትሔዎችን እየሰጠ ይገኛል፡፡ በተጨማሪም በየደረጃው ውይይት በማድረግ ለለውጥ እንቅፋት የሆኑትን የኪራይ ሰብሳቢነት አመለካከትና ተግባራትን ነቅሶ በማውጣት የመፍትሔ እርምጃ ወስዷል፡፡ የሚተላለፉ ውሳኔዎችንም በጋራ በመግባባት እንዲወሰኑና እንዲተገበሩ በማድረግ የጋራ ሀላፊነት እንዲኖር ተደርጓል፡፡

### 3.2. ከዩኒቨርሲቲው ወደ ምርምር ጉዳዮች ም/ፕ/ጽ/ቤት የወረዱ ስትራቴጂያዊ ግቦች፣ ከስትራቴጂያዊ ግቡ የተገኘ ዉጤትና ስትራቴጂያዊ ግቡን ለማሳካት የተከናወኑ አበይት ተግባራት በትኩረት መስክ

**የትኩረት መስክ 2፡ በምርምርና በቴክኖሎጂ ሽግግር መላቅ**

**እይታ1፡ የተገልጋይ/ደንበኛ/ባለድርሻ እይታ**

ግብ1፡ የተገልጋዩን እርካታና ተሳትፎ ማሳደግ

ውጤት፡ ያደገ የተገልጋይ እርካታና ተሳትፎ

ዋና ዋና ተግባራት፡

1. የምርምር ንድፈ ሀሳቦችን አሳታፊ በሆነ መልኩ ለማስገምገምና ለመምረጥ በተያዘው እቅድ መሠረት የእቅዱን 128% ማሳካት ተችሏል፡፡

   በአንደኛው ሩብ አመት ለ2009 ዓ.ም. አዲስ ለሚጀመሩ የምርምር ስራዎች በ2008 ዓ.ም. በወጣው ጥሪ መሠረት የገቡትን 270 የምርምር ንደፈ ሀሳቦች በሁለት ዙር መረጣና የመጨረሻ ደረጃ የማጣጣም ስራ ለማስገምገም በተደረገው ጥረት 86 የምርምር ቡድን አባላትን በማሳተፍ ለማጠናቀቅ ተችሏል፡፡

   በሶስተኛው ሩብ አመት ለ2010 ዓ.ም. አዲስ ለሚጀመሩ የምርምር ስራዎች የአመቱን ቅድሚያ የሚሰጣቸው የምርምር ስራዎች ተለይተው ተመራማሪዎች የምርምር ንድፈ ሃሳባቸውን አዘጋጅተው ያመለክቱ ዘንድ ግልጽ ማስታወቂያ ወጥቷል፡፡

   በዚሁ መሠረት በአራተኛው ሩብ አመት 167 የምርምር ንድፈ ሃሳቦች የገቡ ሲሆን የመጀመሪያ ደረጃ የመረጣ ስራ ተከናውኖ 108 የሚሆኑት ንድፈ ሃሳቦችን በመምረጥ ለሁለተኛ ዙር የመረጣ ስራ ተመራማሪዎች ንድፈ ሃሳቦቻቸውን በመድረክ ላይ አቅርበዋል፡፡ በዚሁ ሁለተኛ ዙር መረጣ ወቅት 55 ልምድ ያላቸውን የምርምር

ቡድን አባላትን (ገምጋሚዎችን) በማሳተፍ ግምገማው የተካሄደ ሲሆን በግምገማው ውጤት መሠረት ንድፈ ሃሳቦቹ ደረጃ ተሰጥቷቸው የሶስተኛውን እና የመጨረሻውን ውጤት ለማሳወቅ በጀት እየተጠበቀ ይገኛል፡፡

ሠንጠረዥ 1 ለ2010ዓ.ም. የቀረቡ የምርምር ንድፈ ሃሳቦች በትኩረት መስክ

| Theme | No. of Submitted Proposals | No. of Proposals Presented for Second Round Screening |
|---|---|---|
| **Theme 1 (Productivity, Emvironmental Sustainability for Food Security and Poverty Alleviation)** | 35 | 30 |
| **Theme 2 (Human Health, Nutrition and Welfare)** | 40 | 20 |
| **Theme 3 (Energy, Engineering and Information Technologies)** | 20 | 9 |
| **Theme 4 (Human and Social Developments)** | 39 | 24 |
| **Theme 5 (Institutions, Innovation Systems and Economic Development)** | 14 | 10 |
| **Theme 6 (Basic Sciences Research)** | 19 | 15 |
| **Total** | **167** | **108** |

2. ፍላጎት ተኮር የቴክኖሎጂ ሽግግር ስራን ለማከናወን በተያዘው እቅድ መሠረት በአመቱ በተለያዩ ወረዳዎች 36 የሚሆኑ ቴክኖሎጂዎች የስርጭት ስራ ተሰርቶ የእቅዱን 86% ማከናወን ተችሏል፡፡

በአንደኛውና በሁለተኛው ሩብ አመት የተለያዩ የተላመዱ የቴክኖሎጂ ዉጤቶችን በማስፋፋት ረገድ መስራች የበቆሎ ዘር በ19 ሄ/ር ፣ ማሽላ በ6 ሄ/ር፣ ስንዴ በ20 ሄ/ር ፣ ለዉዝ በ1 ሄ/ር ፣ ሽምብራ በ12 ሄ/ር ፣ ድንች በ20 ሄ/ር  በድምሩ በ62 ሄ/ር ላይ ተባዝቷል፡፡

በሶስተኛው ሩብ አመት ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ በተያዘው እቅድ መሰረት የካሮትና የሽንኩርት ዝርያዎች በዋናው ግቢ ውስጥ በ0.25 ሄክታር ላይ ተባዝቷል፡፡ እንዲሁም ምርጥ የበቆሎ ዝርያ በሁለት ሄክታር እና አራት አይነት የቦሎቄ ዝርያዎች በአንድ ሄክታር ላይ በድምሩ በሶስት ሄክታር ላይ በበርከሌ የምርምር ጣቢያ የዘር ማባዛት ስራ ተከናውኗል፡፡ በተጨማሪም በዋናው ግቢ በ0.5 ሄክታር ላይ የበቆሎ ዝርያና አንድ ሄክታር ማሳ ላይ የካሮት ዘር ተባዝቷል፡፡



በበርከሌ የምርምር ጣቢያ የዘር ማባዛት ስራ

የተለያዩ የእንስሳት መኖ ዘሮችን በማባዛት የመኖ ዘር ችግርን ለመቅረፍ በድሬዳዋ የቶኒ ፋርም ከ85 ኪ.ግ በላይ የመኖ ዘሮችን ማምረት ተችሏል፡፡




የተለያዩ የእንስሳት መኖ ዘሮች ብዜት ስራ

በዚሁ ሩብ አመት በወቅታዊ የአየር መዛባት ምክንያት በተከሰተው ውርጭ አትክልትና ሰብል ለተበላሸባቸው (ለጠፋባቸው) በሐረማያ ወረዳ ለሰባት ቀበሌዎች ለሚኖሩ አርሶ አደሮች 32 ኩንታል የበቆሎ እና 290 ኩንታል የድንች ምርጥ ዘር ተሰራጭቷል፡፡ በተጨማሪም በውርጬ ለተጎዱና ለምግብ እጥረት ለተጋለጡ አርሶ አደሮች 86 ኩንታል የበቆሎ እህል ተሰጥቷል፡፡



የተለያዩ የሰብል ዝርያዎች ምርጥ ዘር እና የምግብ እህል ስረጭት በከፊል

በአራተኛው ሩብ አመት ደግሞ ሶስት የኦጋዴን ዝርያ ኮርማ የቀንድ ከብት በጉራዋ ወረዳ፤ ዘመናዊ የድንች ዘር ማከማቻ በሐረማያ ወረዳ፤ 10 ዘመናዊ የንብ ቀፎዎች በሐረማያና ጉራዋ ወረዳዎች፤ 3 የእናት ንብ ብዜት በሐረማያ ወረዳ፤ 5 የብርቱኳንና 1 የመንደሪን አይነት በአጠቃላይ 1700 ችግኝ በድሬዳዋና አካባቢው እንዲሁም በሁርሶ ማሰልጠኛ፤ 3 የቲማቲም፣ 1 የጥቅል ጎመን፣ 1 የቀይ ሥርና 1 የቆስጣ ዝርያዎች ሐረማያ፣ ሐረሪና ድሬዳዋ ተሰራጭተዋል፡፡



የብርቱካን ችግኝ በድሬዳዋ ምርምር ጣቢያ



ለጉራዋ አካባቢ የተሰራጩ ኮርማዎች

ሠንጠረዥ 2 በተለያዩ ወረዳዎች የተሰራጩ ቴክኖሎጂዎች በአይነት

| ተ/ቁ | የቴክኖሎጂ አይነት | የዝርያ ብዛት | የተስፋፋበት ቦታ |
|---|---|---|---|
| 1 | በቆሎ | 7 ዝርያዎች | ጭናቅሰን፤ ጉርሱም፤ ሐረማያ፤ ቀርሳ፤ሜታ፤ጎሮ ጉቱ፤ ደደር፤ፌዲስ፤ ባቢሌ፤ ሂርና፤ ኩርፋ ጨሌ፤ ግራዋ፤ ጃርሶ፤ ድሬ ጠያራ፤ ሶፊ፤ ኤረር ወልድያ፤ ኮምቦልቻ |
| 2 | ማሽላ | 8 ዝርያዎች | ጭናቅሰን፤ ጉርሱም፤ ሐረማያ፤ ቀርሳ፤ሜታ፤ጎሮ ጉቱ፤ ደደር፤ፌዲስ፤ ባቢሌ፤ ሂርና፤ ግራዋ፤ ኩርፋ ጨሌ፤ ጃርሶ፤ድሬ ጠያራ፤ ሶፊ፤ ኤረር ወልድያ፤ ሚኤሶ |
| 3 | ስንዴ | 6 ዝርያዎች | ጭናቅሰን፤ ጃርሶ፤ ሐረማያ፤ ሜታ፤ጎሮ ጉቱ፤ ፌዲስ፤ ሂርና፤ ግራዋ |
| 4 | ባቄላ | 3 ዝርያዎች | ሐረማያ፤ ሜታ፤ጎሮ ጉቱ፤ ደደር፤ ሂርና፤ ግራዋ |
| 5 | አተር | 1 ዝርያ | ሐረማያ፤ ሜታ፤ጎሮ ጉቱ፤ ደደር፤ ግራዋ |
| 6 | ድንች | 2 ዝርያዎች | ጭናቅሰን፤ ጉርሱም፤ ሐረማያ፤ ቀርሳ፤ሜታ፤ጎሮ ጉቱ፤ ደደር፤ግራዋ፤ ኮምቦልቻ፤ ድሬ ጠያራ |
| 7 | ጤፍ | 1 ዝርያ | ባቢሌ |
| 8 | ካሮት | 1 ዝርያ | ሐረማያ፤ ሜታ፤ ጎረ ጉቱ፤ ግራዋ፤ ኮምቦልቻ፤ ጭሮ |
| 9 | ነጭ ሽንኩርት | 1 ዝርያ | ሐረማያ፤ ሜታ፤ ጎረ ጉቱ፤ ግራዋ |
| 10 | ለውዝ | 3 ዝርያዎች | ጭናቅሰን፤ ጉርሱም፤ ሐረማያ፤ ቀርሳ፤ፌዲስ፤ባቢሌ፤ ሶፊ፤ ድሬ ዳዋ |
| 11 | ሰሊጥ | 2 ዝርያዎች | ጭናቅሰን፤ ጉርሱም፤ ሐረማያ፤ ቀርሳ፤ፌዲስ፤ባቢሌ፤ ሶፊ፤ ድሬ ዳዋ |
| 12 | ሽምብራ | 2 ዝርያዎች | ሐረማያ፤ ሜታ፤ ጎረ ጉቱ፤ ግራዋ፤ጃርሶ፤ |
| 13 | ስኳር ድንች | 1 ዝርያ | ሐረማያ፤ ሚደጋ ቶላ፤ ድሬ ዳዋ፤ |
| 14 | ጥቅል ጎመን | 1 ዝርያ | ሐረማያ |
| 15 | ቀይ ሽንኩርት | 1 ዝርያ | ሐረማያ |
| 16 | ቬች የእንስሳት መኖ | 1 ዝርያ | ሐረማያ፤ ሜታ፤ ጎረ ጉቱ፤ ግራዋ፤ጃርሶ፤ ፌዲስ፤ ጉርሱም፤ ድሬ ጠያራ፤ ኤረር ወልድያ፤ ሶፊ |
| 17 | ካው ፒ የእንስሳት መኖ | 1 ዝርያ | ሐረማያ፤ ሜታ፤ ጎረ ጉቱ፤ ግራዋ፤ጃርሶ፤ ፌዲስ፤ ጉርሱም፤ ድሬ ጠያራ፤ ኤረር ወልድያ፤ ሶፊ |
| 18 | አልፋ አልፋ የእንስሳት መኖ | 1 ዝርያ | ሐረማያ፤ ሜታ፤ ጎረ ጉቱ፤ ግራዋ፤ጃርሶ፤ ፌዲስ፤ ጉርሱም፤ ድሬ ጠያራ፤ ኤረር ወልድያ፤ ሶፊ |
| 19 | የእርግብ አተር የእንስሳት መኖ | 1 ዝርያ | ሐረማያ፣ ሜታ፣ ጎረ ጉቱ፣ ግራዋ፣ ጃርሶ፣ ፌዲስ፣ ጉርሱም፣ ድሬ ጠያራ፣ ኤረር ወልድያ፣ ሶፊ |
| 20 | ተንቀሳቃሽ የዶሮ ቤት | 1 ቴክኖሎጂ | ሚደጋ ቶላ፤ ሐረማያ፤ ጅግጂጋ |
| 21 | የጠብታ መስኖ ቴክኖሎጂ | 1 ቴክኖሎጂ | ሐረማያ |
| 22 | ዶሮ | 2 ዝርያዎች | ሚደጋ ቶላ |
| 23 | ፍየል | 1 ዝርያ | ሐረማያ፤ ድሬዳዋ |
| 24 | በግ | 1 ዝርያ | ሐረማያ፤ ድሬዳዋ |
| 25 | ሉፒን | 1 ዝርያ | ሜታ፤ ጎሮ ጉቱ፤ ግራዋ፤ ደደር፤ ሂርና |
| 26 | ቦሎቄ | 4 ዝርያዎች | ጉራዋ፣ ሜታ፣ ጎረ ጉቱ፣ ጃርሶ፤ጭናቅሰን |
| 27 | ኮርማ የቀንድ ከብት | የኦጋዴን ዝርያ | ጉራዋ |
| 28 | ዘመናዊ የድንች ዘር ማከማቻ | 1 መጋዘን | ሐረማያ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 29 | የንብ ቀፎ | 1 ቴክኖሎጂ | ሐረማያ፣ ጉራዋ |
| 30 | የእናት ንብ ብዜት | 1 ቴክኖሎጂ | ሐረማያ |
| 31 | የብርቱኳን ችግኝ | 5 ዝርያዎች | ድሬዳዋ፣ ኤረር |
| 32 | የመንደሪን ችግኝ | 1 ዝርያ | ድሬዳዋ፣ ኤረር |
| 33 | ቲማቲም | 3 ዝርያዎች | ሐረማያ፣ ሐረሪ፣ ድሬዳዋ |
| 34 | ጥቅል ጎመን | 1 ዝርያ | ሐረማያ |
| 35 | ቀይ ሥር | 1 ዝርያ | ሐረማያ |
| 36 | ቆስጣ | 1 ዝርያ | ሐረማያ |

3. የምርምር ፋሲሊቲዎችን ለተመራማሪዎች በወቅቱ ለማቅረብ በተያዘዉ እቅድ መሠረት የእቅዱን 100% ማሳካት ተችሏል፡፡ ይህም በመሆኑ ከምርምር ፋሲሊቲዎች አቅርቦት አንጻር ይነሱ የነበሩ ችግሮችን ለመቅረፍ ተችሏል፡፡

4. የምርምር ትኩረት መስክ መሪዎች እና ተመራማሪዎችን በምርምር ፋሲሊቲዎች ማስፋፋት ሂደት ዉስጥ እንዲሳተፉ ለማድረግ በአመቱ የተያዘውን እቅድ 125% ማሳካት ተችሏል፡፡

   በዚህ ዙሪያ አምስት የዉይይት መድረኮች ተዘጋጅተው በምርምር አሰራርና ስራ ላይ ውይይት የተደረገ ሲሆን በተያያዥነትም የመስክ ምልከታ ተደርጓል፡፡



በምርምር ማቢያ የመስክ ምልከታ በከፊል

5. የሴቶችን የልማት ተሳታፊነትንና ተጠቃሚነትን ለማጎልበት በተያዘው እቅድ መሠረት ሴት አርሶ አደሮችን በመስክ ምልከታ፣ በቴክኖሎጂ ስርጭትና በስልጠና ከተሳታፊዎች 10% በላይ እንዲሆኑ በማድረግ የእቅዱን 100% ማሳካት ተችሏል፡፡

## ግብ 2፡ የምርምር አጋርነትንና ትስስርን ማሳደግ

ውጤት፡ ያደገ የምርምር አጋርነትና ትስስር

ዋና ዋና ተግባራት፡

1. ምርምር የሚሹ ችግሮችን ከባለድርሻ አካላት ጋር ለመለየትና ንድፈ ሀሳብ ለመቅረጽ በተያዘው እቅድ መሠረት የእቅዱን 100% ማሳካት ተችሏል፡፡

   በዚሁም መሠረት ከድሬዳዋ ግብርና ቢሮ ጋር በመተባበር በርጥበት አጠር ቦታዎች ሊስፋፉ የሚገቡ ቴክኖሎጂዎችን በመለየት ከዚህ በፊት የግብርና ስራን በዞን ለማስተሳሰርና ለማስተባበር በዚሁም የተሻለ ምርታማነትን ለማረጋገጥ ሲደረግ የነበረውን ጥረት በማደስ በጋራ ለመንቀሳቀስ የዝግጅት ምዕራፍ ተጠናቆ ወደ ስራ ተገብቷል፡፡ እንዲሁም የአየር ንብረት ለውጥን ከግምት ውስት ያስገባ የድንች ምርጥ ዘር ማውጣትና በዝናብ አጠር ቦታዎች ለማሰራጨት ከተመራማሪዎች እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር ውይይት የተደረገ ሲሆን ስራውም ተጀምሯል፡፡

በተጨማሪም የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ የምርምር ቡድን አራት አባላት ታህሳስ 18/2009 ዓ.ም. በሀረሪ ህ/ብ/ክ መንግስት የሀረሪ ባህል እና ቱሪዝም፣ የጤናና የትምህርት ቢሮዎች ጋር በኢንፎርሜሽን እና ቴክኖሎጂ ዘርፍ ምርምር በሚሹ ጉዳዮች ዙሪያ ሰፋ ያለ ውይይት ተደርጓል፡፡ በዚሁ መሠረት በመረጃ አያያዝና አጠቃቀም፤ ፈጠራ የታከለበት ድህረ-ገፅ ዝግጅት፤ ስልጠና (በሶፍት ዌር አጠቃቀም፣በመረጃ አያያዝ ፣ በስታስቲክስ ሶፍት ዌር አጠቃቀም) እና ሙዚየምንና ቤተ-መጻህፍትን ማዘመን (Digitalization) ከዩኒቨርሲቲው ጋር በጋራ ለመስራት ስምምነት ተደርሷል፡፡

ከምርምርና ኢንዱስትሪ ተቋማት፣ ከሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚንስቴር፣ ከኢትዮጵያ የጨርቃጨርቅ ኢንዱስትሪ ማበልፀያ እና ከኢትዮጵያ ቆዳ ኢንዱስትሪ ማበልፀጊያ ተቋማት ጋር ትኩረት የሚሹ እና በጋራ ምርምር የሚደረግባቸው ዋና ዋና ችግሮች (የአካባቢ ብክለትን መከታተልና መከላከል (Environmental monitoring and remediation)፣ የጨርቃጨርቅ ማቅለሚያ ቀለሞች እንዳይለቁ ማስቻል (Textile dyes stabilization)፣ የጨርቃ ጨርቅ ክሮች ላይ (textile fibers) እና በቆዳ ጥራት ጥበቃ ዙሪያ (Improving leather quality including animal husbandry)) ተለይተዋል፡፡

2. ከኢንደስትሪዎች ጋር የምርምር ትብብር ለመፍጠር በተያዘው እቅድ መሠረት 80% የአመቱን እቅድ ማሳካት ተችሏል፡፡

   ከአዳማ የብረታ ብረትና ኢንጅነሪንግ የእርሻ መሳሪያዎች ድርጅት Agro-processing የምርምር መስክ በጋራ ለመስራት በተስማማው ውል መሰረት ንድፈ ሀሳብ ተቀርጾ በሐረርጌ ለሚኖረው ማህበረሰብ እንደሚጠቅም ስለታመተነት ቆጮን ከእንሰት ለማዘጋጀት ታቅዷል፡፡

   በሶስተኛው ሩብ አመትም በመሠረታዊ ሳይንስ የምርመር ትኩረት አቅጣጫ ከተለያዩ ተቋማት ጋር ትብብር ለመፍጠር በታቀደው መሠረት ከኢትዮጵያ ብዝኃ-ህይወት ተቋም ጋር በብዝኃ-ህይወት ምርምር ስራ ላይ በጋራ ለመስራት ሁኔታዎች ተመቻችተዋል፡፡

3. በስድስቱ የምርምር ትኩረት መስኮች ትኩረት የሚሹ የምርምር ፍላጎቶችን ዳሰሳ ጥናት ለማካሄድ በተያዘው እቅድ መሠረት የአመቱን 60% ብቻ ማከናወን ተችሏል፡፡

   የሰብል በሽታዎችን ስርጭትና የሚያስከትሉትን ተጽኖ ለማወቅ በምስራቅ ሐረርጌ በሚገኙ የተለያዩ ወረዳዎች ላይ የዳሰሳ ጥናት ተካሂዶና የመፍትሄ አቅጣጫ ተቀምጦ አስፈላጊው እርምጃ በባለድርሻ አካላት እንዲወሰድ ተደርጓል፡፡ በሶስተኛው ሩብ አመትም በተቋማት፣ ኢኖቬሽን ሲስተምስ እና ኢኮኖሚ ልማት የምርምር ትኩረት አቅጣጫ ስር ምርምር የሚሹ ችግሮችን ለመለየት በተካሄደው አውደ ጥናት ጠቃሚ ተሞክሮዎች ተገኝተዋል፡፡ በአራተኛው ሩብ አመት ደግሞ በተለዩት ችግሮች ላይ ንድፈ ሃሳቦች ተዘጋጅተውና ተገምግመው ለትግበራ ዝግጁ ሆነዋል፡፡

4. ከባለድርሻ አካላት ጋር ለስርጸት የሚሆን ቴክኖሎጂዎችን ማዘጋጀትና እንዲሰራጩ ለማድረግ በተያዘው እቅድ መሠረት የእቅዱን 233% ማከናወን ተችሏል

   ZOA| Relief|Hope|Recovery ከሚባል አለማቀፍ ድርጅት ጋር በመተባበር ተንቀሳቃሽ የዶሮ ቤትና እንቁላል ጣይ ዶሮዎች በሚደጋ ቶላ ወረዳ ተሰራጭተዋል፡፡ እንዲሁም ከድሬዳዋ መስተዳደርና ከሐረማያ ወረዳ የእንስሳትና እና አሳ ሀብት ልማት ጋር በመቀናጀት የተሻሻሉ የፍየልና በግ ዝርያዎች ተሰራጭተዋል፡፡ በተጨማሪም ከተቀናጀ ዘር ልማት ፕሮግራም (BENEFIT-ISSD) ጋር በመተባበር የተለያዩ የሰብል እና የአትክልት ዘር ብዜት ስራዎች እና ከአርብቶ አደር ልማት ፕሮጀክት (PCDP) ጋር በመተባበር ሶስት የስንዴ ዝርያዎች፣ አምስት የማሽላ ዝርያዎችና ሶስት የበቆሎ ዝርያዎች የማስተዋወቅ ስራዎች እየተሰሩ ነው፡፡

በተጨማሪም ከተለያዩ ድርጅቶች ጋር በመተባበር 1.7 ሚሊዮን በላይ የስኳር ድንች ቁርጥራጭ ለ3841 አርሶ አደሮች ተሰጥቷል፡፡



የስኳር ድንች ቁርጥራጭ

በአንደኛው ሩብ አመት የተሻሻሉ የፍየልና በግ ዝርያዎችን ለማስተዋወቅ በተያዘው እቅድ መሠረት የአነስተኛ አመንዣጊ እንስሳት የስጋ ምርት ጥራትና ብዛት ለማሻሻል ከደቡብ አፍሪካ የመጡ የቦር ፍየሎችን እና የዶርፐር በጎችን ከአካባቢው የተመረጡ እንስት ፍየሎች ጋር በማዳቀል 50% ድቃይ ፍየልና በጎችና ከድሬዳዋ ግብርና ቢሮ ጋር በመተባበር 40 የተዳቀሉ ፍየሎችንና 10 የተዳቀሉ በጎች ለማሰራጨት ተችሏል፡፡በአራተኛው ሩብ አመት ለቢሮው 20 ፍየሎችና 20 በጎች ተሰራጭተዋል፡፡ በአጠቃላይ በድምሩ 60 የተዳቀሉ ፍየሎች እና 30 የተዳቀሉ በጎች ተሰራጭተዋል፡፡



የተሰራጩ ፍየሎች እና በጎች

በሶስተኛው ሩብ አመት ዩኒቨርሲቲው ከሐረሪ ክልል እና ድሬዳዋ መስተዳድር ግብርና ልማት አማካሪ ካውንስል ጋር በመተባበር የጋራ መድረክ በማዘጋጀት የምርምር እና ስረጸት ሰራ ላይ የመነሻ ጽሁፍ ቀርቦ ውይይት ተደርጓል፡፡ በዚሁ መድረክ ላይም የጋር መግባባት ተደርሶ ወደስራ ተገብቷል፡፡ በአራተኛው ሩብ አመት ከCare Ethiopia እና HCS ከሚባሉ ድርጅቶች ጋር በመተባበር 817,000 የስኳር ድንች ቁርጥራጭ ተባዝቶ በምስራቅና ምዕራብ ሐረርጌ ለሚገኙ 1,634 አርሶ አደሮች ተሰራጭቶ 408.5 ሄክታር መሬት መሸፈን ተችሏል፡፡

በተጨማሪም ከፌዲስ ግብርና ምርምር ማዕከል እና ከBENEFIT-ISSD ጋር በመተባበር 37,500 የስኳር ድንች ቁርጥራጭ በአርሶ አደር ማሰልጠኛ ማዕከላት ተሰራጭቶ አጥጋቢ ውጤት ስላሳየ በዚሁ ሩብ አመት 53157 ቁርጥራጭ ለስርጭት ተዘጋጅቷል፡፡



ስኳር ድንች ዘር ዝግጅት በድሬዳዋ ምርምር ጣቢያ

ሠንጠረዥ 3 ከተባባሪ ድርጅቶች ጋር በመሆን የተሰራጩ የስኳር ድንች ቁርጥራጭ ብዛት

| ተ/ቁ | ዞን | የተባባሪ ድርጅት ስም | ወረዳ | የአርሶ አደር ብዛት | የስኳር ድንች ቁርጥርጭ ብዛት |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ምዕራብ ሐረርጌ | Care Ethiopia | ዶባ፣ ጭሮ፣ ኦዳ ቡልቱም፣ ቦኬ | 2,714 | 1,557,000 |
| 2 | ምስራቅ ሐረርጌ | ZOA | ሚደጋ ቶላ | 500 | 250,000 |
| | | HCS | ሚደጋ ቶላ እና ፌዲስ | 605 | 302,500 |
| | | ሐረማያ ወረዳ መስኖ ልማት ጽ/ቤት | ሐረማያ | 890 | 445,000 |
| 3 | ምዕራብ እና ምስራቅ ሐረርጌ | BENEFIT-ISSD | ዶባ፣ ጭሮ፣ ኦዳ ቡልቱም፣ ቦኬ | 585 | 292,500 |
| 4 | ምስራቅ ሐረርጌ | BENEFIT-ISSD እና ፌዲስ ግብርና ምርምር ማዕከል | - | አርሶ አደር ማሰልጠኛ ማዕከላት | 37,500 |
| | ድምር | 4 | 8 | 5294 | 2,884,500 |

በተጨማሪም በዚሁ አመት InnovAfrica በተባለው ፕሮጀክት ውስጥ በመሳተፍ ከአውሮፓ ህብረት የግብርና ቴክኖሎጂ ስርጭትን ለማሳለጥ የሚረዳ የገንዘብ ድጋፍ ተገኝቷል፡፡

## ግብ 3፡ ፍላጎት ተኮር የምርምር ውጤቶችን ማሳደግ


**ውጤት፡ ያደገ ፍላጎት ተኮር የምርመር ውጤቶች**

**ዋና ዋና ተግባራት፡**

ፍላጎት ተኮር የምርምሮችን ለመከታተል፣ ለመደገፍና ለማጠናቀቅ በተያዘው እቅድ መሠረት የእቅዱን 100% ማከናወን ተችሏል፡፡ ይህም በምርምር ትኩረት መስክ እንደሚከተለው ተብራርቷል፡፡

1. በ "Productivity, Environmental Sustainability for Food Security and Poverty Alleviation" የምርምር ትኩረት አቅጣጫ ስር ምርምሮችን ለማካሄድ፣ ለመከታተልና ለመደገፍ በተያዘው እቅድ መሰረት በዩኒቨርሰቲው መደበኛ በጀት እና አጋር አካላት የሚካሄዱ 49 የምርምር ፕሮጀክቶችን (194 የምርምር ስራዎች) መከታተል እና መደገፍ ተችሎአል፡፡ ከነዚህም ውስጥ በ2008 ዓ.ም የተጀመሩ 16 ፕሮጀክቶች፣ በ2009 ዓ.ም የተጀመሩ 14 ፕሮጀክቶች እና በኢትየጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት ድጋፍ የሚደረግላቸው 18 ቋሚ ፕሮጀክቶች ክትትልና ድጋፍ የተደረገላቸው ሲሆን፣ ከነዚህም ውስጥ በለውዝ ጥናት በሀገሪቱ ሐረማያ ዩኒቨርስቲ የሚያስተባብረው ነው፡፡ ከነዚህ የምርምር ስራዎች ውስጥ ሁለት የሰሊጥ ዝርያዎች እና ሶስት የለውዝ ዝርያዎች በዘር አጽዳቂ ኮሚቴ ተገምግመው ጸድቀው ተለቀዋል፡፡

ሠንጠረዥ 4 በ2009 ዓ.ም. የሰብል ዝርያዎች

| Two sesame varieties |  |  |
|---|---|---|
| **Particulars** | BaHa-zeyit | BaHa-necho |
| Adaptation | Eastern part of Ethiopia (Gursum, Babile, Bisidimo and similar agro-ecologies in Ethiopia) | Gursum, Babile, Bisidimo and similar agro-ecologies in Ethiopia) |
| Research field (Qt $ha^{-1}$) | 13 | 12 |
| Farmers' field (Qt $ha^{-1}$) | 10-13 | 8-12 |

| **Groundnut varieties** | | |
|---|---|---|
|  |  |  |
| **Babile-1** (ICGV-98412) | **Babile-2** (ICGV-98404) | **Babile-3 (ICGV-94100)** |
| 24 qt/ha | 20 qt/ha | 24 qt/ha |

በተጨማሪም የተለያዩ የስንዴ ዝርያዎች ለአገር አቀፍ ዘር አጽዳቂ ኮሚቴ ቀርበው የተገመገሙ ሲሆን የዩኒቨርሲቲው የስንዴ ተመራማሪዎችም በአገር አቀፍ ደረጃ ውጤቱን አቅርበው ማብራሪያ ሰጥተው አስገምግመዋል፡፡ በአሁኑ ጊዜ የዘር አጽዳቂ ኮሚቴ ውሳኔ እየተጠበቀ ይገኛል፡፡


የዘር አጽዳቂ ኮሚቴው በመስክ ላይ

በሶስተኛው ሩብ አመትም ይኸው ስራ ተጠናክሮ የቀጠለ ሲሆን ሶስት የሰብል ዝርያዎችን ለማጸደቅና ለማስመዝገብ በተደረገው ጥረት አንድ የዳቦ ስንዴ፣ አንድ የበቆሎ እና አንድ የሽንኩርት ዝርያ ግምገማ ተካሂዶባቸዋል፡፡

በሶስተኛው ሩብ አመት ተገምግመው የነበሩት ሁለት የበቆሎ ዝርያዎች በአራተኛው ሩብ አመት ጸድቀው ኦፊሴላዊ ደብዳቤ እየተጠበቀ ይገኛል፡፡ በተጨማሪም በሀገራዊ ዝርያ አጽዳቂ ኮሚቴ የተገመገመውን አንድ

የቀይ ሽንኩርት ዝርያ ተመራማሪዎች በአገር አቀፍ ደረጃ ውጤቱን በማቅረብ ማብራሪያ ሰጥተው አስገምግመዋል፡፡ በአሁኑ ጊዜ የዘር አጽዳቂ ኮሚቴ ውሳኔ እየተጠበቀ ይገኛል፡፡

2. በ “Human Health, Nutrition and Welfare” የምርምር ትኩረት አቅጣጫ ስር ምርምሮችን ለማካሄድ፣ ለመከታተልና ለመደገፍ በተያዘው እቅድ መሰረት በዩኒቨርሰቲው ድጋፍ የሚደረግላቸው 30 የምርምር ፕሮጀክቶችን (75 የምርምር ስራዎች) መከታተል ተችሏል፡፡ ከዚህም ውስጥ በ2008 ዓ.ም የተጀመሩ 16 ፕሮጀክቶች ሲሆኑ በ2009 ዓ.ም የተጀመሩ 14 ፕሮጀክቶች ክትትል ማድረግ ተችሎአል፡፡በ Human Health, Nutrition and Welfare የምርምር ትኩረት አቅጣጫ ስር ዩኒቨርሲቲው ለ2009 የምርምር ንድፍ ሐሳብ ባወጣው ጥሪ መሰረት የቀሩበትን 75 የምርምር ንድፈ ሀሳቦችን አሳታፊ በሆነ መልኩ በማስገምገምና በመመረጥ 16 የምርምር ፕሮጀክቶችን በመለየት የተመደበላቸውንም በጀት በማሳወቅ ወደ ምርምር ስነ-ምግባር ማስተባበሪያ ቢሮ እንዲላኩና እንዲገመገሙ በማድረግ አስፈላጊውን ድጋፍ ተደርጓል ፡፡ በምርምር ንድፈ ሀሳቦች መረጣና በጀትምደባ ላይ የተነሱትን እንዳንድ የመምህራን ቅሬታዎችና ጥያቄዎችንም አግባብ ባለው መልኩ ለማስተናገድተችሏል፡፡ በተጨማሪም የ2015-16 የምርምር ውጤት ሪፖርቶች ተጠናቀው እንዲቀርቡ በቃልናበፅሁፍ ማስታወቂያ በመለጠፍ ለማስገንዘብ ተችሏል፡፡የስራ ላይ ስልጠና ለመስጠት (on job Training) በታቀደውመሰረት የመምህራንንና የPhD ተማሪዎችን የምርምር አቅምን ለማሻሻል ከHarvard University ጋር በመተባበር “Applied Longitudinal Data Analysis” በሚል ርእስከ January 5-6/2017 ለ34 መምህራንንና ተማሪዎች ስልጠና ተሰጥቶአል፡፡



የስራ ላይ ስልጠና

3. በኢነርጂ፣ ኢንጅነሪንግና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ የምርምር ትኩረት አቅጣጫ ስር በ2009 ዓ.ም. በጀት የሚካሄዱ 12 አዳዲስና 14 ከባለፉት አመታት የቀጠሉ በጠቅላላው 26 የምርምር ፕሮጀክቶችን ለመከታተልና ለመደገፍ በተያዘው እቅድ መሠረት ከአዳዲሶቹ ውስጥ ዘጠኙ ውል ፈርመው የምርምር ስራቸውን ጀምረዋል፡ ፡ ከባለፈው ዓመት የቀጠሉ 14 ፕሮጀክቶች ውስጥ በሁለተኛው ሩብ አመት 5ቱ ተጠናቀው 1 ፕሮጀክት ደግሞ ተቋርጧል፡፡ በዚህ ሩብ ዓመት ደግሞ 2 ፕሮጀክት ተጠናቋል፡፡

a) Nanomaterial synthesis and characterization for various applications፡ በዚህ የምርምር ስር የሚካሄዱ 4 ፕሮጀክቶች ሲሆኑ በአጠቃላይ 17 የማስተርስና 1 የዶክትሬት ድግሪ ተማሪዎች ተሳትፈዋል፡፡ ከነዚህም ውስጥ 3 የማስተርስ ተማሪዎች በሶስተኛው ሩብ አመት ምርምራቸውን አጠናቀው የመመረቂያ ፅሁፋቸውን አቅርበዋል፡፡ GRO/PANI/ZnO, GRO/PANI/Ag, Ag-nanoparticle በማዘጋጀት መርዛማ ብረቶችን፣ የማላታይን መጠን ለማወቅ እንደሚረዳና ባዮሎጂካዊ መንገድ Ag-nanoparticle በማዘጋጀት ባክቴሪያን እና ፈንገስን እንዴት መቋቋም እንደሚቻል አሳይቷል፡፡ Ag- nanoparticle ባክቴሪያዎችን በመግደል ለተለያዩ ጥቅሞች እንደሚውል አሳይተዋል፡፡ ሌሎች 9 ተማሪዎች ምርምሮችን በማካሄድ ላይ ይገኛሉ፡፡

b) Novel value added product፡ የሙዝ ጃም፤ አቮካዶ አይብ፤ የቲማም ከቻፕ ምርቶች ተዘጋጅተው ሳይበላሹ ሊቆይ የሚችሉበት ጊዜ በመጠናት ላይ ነው::

c) Detection of aflatoxin፡ የተለያዩ ናሙናዎች ከተለያ ስፍራዎች ተሰብስበው ቤተ-ሙከራ ውስጥ ምርምር እየተደረገባቸው ይገኛል፡፡

በሶስተኛውና በአራተኛው ሩብ አመት በዚህ የምርምር ትኩረት መስከ 55 ዋና ተመራማሪ መምህራንና ተባባሪ መምህራኖችን እንዲሁም የማስተርስና የዶክትሬት ድግሪ ተማሪዎች 9 በ"Nanomaterial synthesis

and characterization for various applications፣ Cactus pear in food formulation"፣ 2 ተማሪዎች በ"Injera Processing Mech" 2 ተማሪዎች በ"Nobel value added products" ምርምሮች ተሳታፊ ሆነዋል፡፡

ሠንጠረዥ 5 በኢ.ኢ.ኢ.ቴ የምርምር ትኩረት መስክ የተሳተፉ ተመራማሪዎች

| | በምርምር የሚሳተፉ | ወንድ | ሴት | ድምር |
|---|---|---|---|---|
| 1 | መምህራን | 54 | 1 | 55 |
| 2 | የማስተርና የዶክትሬት ድግሪ ተማሪዎች | 13 | 2 | 15 |

4. በ“Human and Social Development” የምርምር ትኩረት አቅጣጫ ስር በዩኒቨርሰቲው ድጋፍ የሚደረግላቸው 16 የምርምር ፕሮጀክቶች (27 የምርምር ስራዎች) መከታተል ተችሏል፡፡ ከዚህም ውስጥ በ2008ዓ.ም የተጀመሩ 8 ፕሮጀክቶች፣ በ2009 ዓ.ም የተጀመሩ 8 ፕሮጀክቶች ናቸው፡፡

5. በ“Institutions, Innovations Systems, and Economic Development” የምርምር ትኩረት አቅጣጫ ስር በዩኒቨርሲቲው ድጋፍ የሚደረግላቸው 11 ፕሮጀክቶችን (30 የምርምር ስራዎችን) መከታተልና መደገፍ ተችሏል፡፡ በዚህ የምርምር ትኩረት መስክ ስር ከተከናወኑት ምርምሮች ለኢንተርፕራይዝ ልማትና ሽግግር፣ ለዘርፈ ብዙ የከተማ ድህነት ቅነሳና ለከተማ-ገጠር ትስስር የሚረዱ የፖሊሲ አቅጣጫዎች ተመላክተዋል፡፡

6. በ“Basic Sciences Research” የምርምር ትኩረት አቅጣጫ ስር በዩኒቨርሲቲው ድጋፍ የሚደረግላቸው 15 ፕሮጀክቶች (23 የምርምር ስራዎች) መከታተል ተችሏል፡፡ በ2008ዓ.ም 8 እና በ2009ዓ.ም የተጀመሩ 7 ፕሮጀክቶች ይገኛሉ፡፡

በሶስተኛው ሩብ አመት ይኸው ስራ ተጠናክሮ ቀጥሏል፡፡ በምርምር ትኩረት አቅጣጫውም በስራ ላይ ያሉትን ምርምሮች ለመገምገም የጋራ የምክክር መድረክ ተዘጋጅቶ ተመራማሪዎች ስራዎቻቸውን እንዲያቀርቡ እና እንዲያስገመግሙ ተደርጓል፡፡ በወቅቱም ተመራማሪዎች የምርምር በጀትን በአግባቡ ጥቅም ላይ ማዋላቸውን ለማወቅ የተከናወኑት ስራዎች ጋር ሪፖርታቸዉን በማየት እና በማነጻጸር ክትትል ለመገምገም ተችሏል፡፡ በሚከተለው ምስል በቀረበው መሰረትም ስራዎቻቸውን በሴሚናር መልክ እንዲያቀርቡ ተደርጓል፡፡



በምርምር የትኩረት መስክ 6 ተመራማሪዎች ስራዎቻቸውን ሲያቀርቡና ሲከታተሉ

በአጠቃላይ በአመቱ በሁሉም የምርምር ትኩረት መስኮች በድምሩ 77 አዲስ የተጀመሩ የምርምር ስራዎች ሲኖሩ በድምሩ 353 ተመራማሪዎችን ያሳተፉ ስራዎች እየተሰሩ ነው፡፡ ከዚህ ውስጥ 35ቱ ሴት ተመራማሪዎች ናቸው፡፡ ከነዚህ ሴቶች መካከል ስድስቱ የምርምር ፕሮጀክቱ መሪዎች ሲሆኑ 29 ደግሞ በተለያዩ ምርምሮች ተሳታፊዎች ናቸው፡፡

ሠንጠረዥ 6 የምርምር ፕሮጀክቶች በትኩረት መስክና በጾታ

| Characteristics | | Sex | | Total |
|---|---|---|---|---|
| | | Male | Female | |
| Projects by theme | I | 15 | 1 | 16 |
| | II | 14 | 3 | 17 |
| | III | 13 | 0 | 13 |
| | IV | 11 | 1 | 12 |
| | V | 10 | 1 | 11 |
| | VI | 8 | 0 | 8 |
| | **Total** | **71** | **6** | **77** |
| Researchers by level of engagement | PI | 71 | 6 | 77 |
| | CO-Investigator | 247 | 29 | 276 |
| | **Total** | **318** | **35** | **353** |
| Researchers by theme distribution | Theme 1 | 79 | 9 | 88 |
| | Theme 2 | 81 | 18 | 99 |
| | Theme 3 | 48 | 2 | 50 |
| | Theme 4 | 42 | 4 | 46 |
| | Theme 5 | 36 | 2 | 38 |
| | Theme 6 | 32 | 0 | 32 |
| | **Total** | **318** | **35** | **353** |

ሠንጠረዥ 7 የምርምር ፕሮጀክቶች በትኩረት መስክና በሁኔታ

| S.N. | Theme | No. of Research Activities | | | | Remark |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | Total | Completed | Ongoing | Discontinued | |
| **1** | Theme 1 | 334 | 50 | 284 | 0 | Additional 30 activities have been temporarily approved to be funded by EIAR. |
| **2** | Theme 2 | 45 | 20 | 25 | 0 | - |
| **3** | Theme 3 | 26 | 8 | 16 | 4 | Agreement was not signed for 3 activities and the PI left for PhD study for the remaining activities. |
| **4** | Theme 4 | 34 | 12 | 15 | 7 | Some researchers left the campus. |
| **5** | Theme 5 | 31 | 8 | 16 | 2 | The Status of 5 activities are unknown as they are handed over to Oda Bultum University |
| **6** | Theme 6 | 23 | 0 | 23 | 0 | The completion report of 50% of the projects is expected to be submitted within one month. |
| **Total** | | **493** | **98** | **379** | **13** | |

ፍላጎት ተኮር የምርምር ውጤቶችን ለማሳደግ በጠቃላይ በአመቱ ሶስት የፈጠራ ስራ ለሚሰሩ ተመራማሪዎች የበጀት ዲጋፍ ተደርጓል፡፡በዚሁ መሰረት ዘርን በመስመር የሚዘራ ቴክኖሎጂ በሙከራ ደረጃ ላይ ይገኛል፡፡



ዘርን በመስመር የሚዘራ ቴክኖሎጂ በሙከራ ላይ

## ግብ 4፡ የምርምር ቴክኖሎጂ ሽግግር እና ሀትመትን ማሳደግ

ውጤት፡ የተሻሻለ የቴክኖሎጂ ሽግግርና ሀትመት

**ዋና ዋና ተግባራት፡**

1. በአርሶ አደር ማሰልጠኛ ማዕከላት አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን በሰርቶ ማሳያ ለመስራትና ለመምረጥ በተያዘዉ እቅድ መሠረት የእቅዱን 100% ማሳካት ተችሏል፡፡

ሠንጠረዥ 8 የቴክኖሎጂዎች ስርጭት በወረዳና በአርሶ አደር ማሰልጠኛ ማዕከል

| ተ.ቁ | ወረዳ | የማሰልጠኛ ብዛት | የቴክኖሎጂ አይነት |
|---|---|---|---|
| 1 | ሐረማያ | 17 | ማሽላ፣ በቆሎ፣ ድንች፣ ካሮት፣ የእንሳት መኖ፣ ለውዝ፣ ቦሎቄ፣ ነጭ ሽንኩርት |
| 2 | ቀርሳ | 3 | ማሽላ፣ በቆሎ፣ ድንች፣ ካሮት፣ የእንሳት መኖ፣ ለውዝ |
| 3 | ሜታ | 2 | ማሽላ፣ በቆሎ፣ ድንች፣ ካሮት፣ የእንሳት መኖ፣ ለውዝ፣ ነጭ ሽንኩርት፣ ሉፒን፣ ስኳር ድንች |
| 4 | ጎሮ ጉቱ | 3 | ማሽላ፣ በቆሎ፣ ድንች፣ ካሮት፣ የእንሳት መኖ፣ ቦሎቄ፣ባቄላ፣ ሉፒን፣ አተር |
| 5 | ደደር | 2 | ማሽላ፣ በቆሎ፣ ድንች፣ ባቄላ፣ ሉፒን፣ አተር |
| 6 | ጉራዋ | 2 | ማሽላ፣ በቆሎ፣ ድንች፣ ካሮት፣ የእንሳት መኖ፣ ቦሎቄ፣ባቄላ፣ ሉፒን፣ አተር፣ ስንዴ፣ ነጭ ሽንኩርት |
| 7 | ኩርፋ ጨሌ | 2 | ማሽላ፣ በቆሎ |
| 8 | ድሬ ደዋ | 2 | ማሽላ፣ በቆሎ፣ ለውዝ |
| 9 | ፌዲስ | 3 | ማሽላ፣ በቆሎ፣ የእንሳት መኖ፣ ሰሊጥ፣ ለውዝ |
| 10 | ባቢሌ | 2 | ማሽላ፣ በቆሎ፣ ሰሊጥ፣ ለውዝ፣ ጤፍ |
| 11 | ጉርሱም | 2 | ማሽላ፣ በቆሎ፣ የእንሳት መኖ፣ ሰሊጥ፣ ለውዝ |
| 12 | ጃርሶ | 4 | ማሽላ፣ በቆሎ፣ ድንች፣ የእንሳት መኖ፣ ቦሎቄ፣ ባቄላ፣ አተር |
| 13 | ጭናክሰን | 2 | ማሽላ፣ በቆሎ፣ ሰሊጥ፣ ለውዝ፣ ቦሎቄ፣ ድንች፣ ስንዴ |
| 14 | ኮመቦልቻ | 1 | ቦሎቄ፣ በቆሎ፣ ካሮት |
| 15 | ድሬ ጠያራ | 1 | ማሽላ፣ በቆሎ፣ ድንች፣ የእንሳት መኖ |
| 16 | ሶፊ | 2 | ማሽላ፣ በቆሎ፣ ድንች፣ የእንሳት መኖ፣ ለውዝ |
| | ድምር | 50 | |

በሁለተኛው ሩብ አመት በነዚሁ የአርሶ አደር ማሰልጣኛ ተቋማት እየተካሄዱ ያሉትን ስራዎች በመከታተል አስፈላጊውን መረጃ የማሰባሰብ ስራ ተሰርቷል፡፡



የአርሶ አደር ማሰልጣኛ ተቋማት ላይ የተመረተ



በኤረር ወልዲያ የፍየል ማዳቀል ስራ በከፊል

በአራተኛው ሩብ አመት ደግሞ በ2009/10ዓ.ም. የምርት ዘመን ሊሰራባቸው የሚገባ የአርሶ አደር ማሠልጠኛ ማዕከላትን ለመለየት የዳሰሳ ጥናት የተካሔደ ሲሆን በዚሁ መሠረት 50 ማዕከላት ተመርጠው ከነዚህም ውስጥ ዘጠኙን ወደ ሞዴል ማዕከልነት ለማሳደግ ታቅዷል፡፡ በዚሁ ሩብ አመት የበቆሎ፣ የድንች፣ የማሽላ፣ የስንዴ፣ የለውዝ፣ የካሮት፣ የነጭ ሽንኩርት፣ የቦሎቄ፣ የአተር እና የተለያዩ የእንስሳት መኖ ዘሮች ለሃምሳዎቹም የአርሶ አደር ማሠልጠኛ ማዕከላት እንደየስነ-ምህዳሩ ሁኔታ ተሰራጭተው የክትትል ስራ እየተደረገ ነው፡፡

3. የተሻሻሉ ቴክኖሎጂዎችን በሰርቶ ማሳያ ለማስተዋወቅ በተያዘው እቅድ መሠረት የእቅዱን 137% ማከናውን ተችሏል፡፡

በዚሁ መሠረት የንብ፣ የፍየል፣ የበግ፣ የዶሮ እና የዶሮ ቤት ቴክኖሎጂዎችን ማስተዋወቅ ተችሏል፡፡ ከተዋወቁት ቴክኖሎጂዎች ውስጥ 14 ባለሶስት ደረጃ ተንቀሳቃሽ የዶሮ ቤቶች ለሐረማያ ወረዳ እንስሳትና አሳ ሃብት ጽ/ቤት ማቅረብ ተችሏል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በ2008ዓ.ም የተሰራጨትን የዶሮ ዝርያዎች በመጠቀም በቢፍቱ ገዳ የገጠር ቀበሌ በሶስት አርሶ አደሮች ላይ አስር አስር የኳይት ሌግ ሆርን እንቁላሎች በማስታቀፍና በማስፈልፈል ዝርያው በአርሶ አደሮች እንዲዳረስ አስተዋጾ ተደርጓል፡፡

በሶስተኛው ሩብ አመት በኢፋ ኦሮሚያ እና ቢፍቱ ገዳ አርሶ አደር ማሰልጠኛ ማእከልና በጢኒቄ ሞዴል አርሶ አደር ማሳ ላይ የውሃ ቆጣቢ መስኖ ስራ የማስተዋወቅ ስራ ተሰርቷል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በቢፍቱ ገዳ የአርሶ አደር ማሰልጠኛ ማዕከል ላይ የእናት ንብ ማባዛት ስራ፤ የእንቁላል ጣይ ዶሮዎች እና የተሻሻሉ የፍየል ዝርያዎች የማስተዋወቅ ስራ ተከናውኗል፡፡



የጠብታ መስኖ የማስተዋወቅ ስራ በተለያዩ የአርሶ አደር ማሰልጠኛ ተቋማት በከፊል

በሶስተኛው ሩብ አመት ሶስት የዶሮ ዝርያዎች (ኮኮክ፤ ሬድ በርድ፤ እና ሶሴክስ) ከደብረ ዘይት የምርምር ማእከል አምስት መቶ ጫጩቶችን በማምጣትና በማላመድ ለስርጭት ዝግጁ ሆነው በአራተኛው ሩብ አመት ጫጩቶቹ የሶስት ወር እድሜ የሞላቸው ሲሆን ስርጭቱን ለማከናወን ይረዳ ዘንድ የአርሶ አደር መረጣና ለስርጭቱ የሚያገለግል የቁሳቁስ ግዢ ተፈጽሞ የግንባታው ስራ ሂደት ተጀምሯል፡፡



ለስርጭት በዝግጅት ላይ ያሉ የዶሮ ዝርያዎች በከፊል

በተጨማሪም በማህበረሰብ ተኮር ልማት ዳይሬክቶሬት ጋር በመተባበር 101 አንደኛ ደረጃ 15 ዶሮዎች የሚይዝ ተንቀሳቃሽ የዶሮ ቤት ተሰርቶ በሐረማያ ዙሪያ ላሉ የማህበረሰብ አባላት የተሰራጨ ሲሆን አራት ባለሶስት ደረጃ 45 ዶሮዎች የሚይዝ ተንቀሳቃሽ የዶሮ ቤት ተሰርቶ ለኦዳ ቡልቱም ዩኒቨርሲቲ ለቴክኖሎጂ ሽግግር እንዲያገለግል ተሰጥቷል፡፡ እንዲሁም ከተለያዩ አርሶ አደሮች በመጡ ጥያቄዎች መሠረት 25 ባለአንድ ደረጃ ቤቶች ተሰርተው ተከፋፍለዋል፡፡

4. የተሻሻሉ ቴክኖሎጂዎች በዩኒቨርሲቲው ማዕከላት፣ በኩታ ገጠም አርሶ አደር ማሳዎችና በዘር አምራች ማህበራት ለማባዛት በተያዘው እቅድ መሠረት የእቅዱን 138% ማከናወን ተችሏል፡፡

በመጀመሪያው ሶስት ሩብ አመት 4205.7 ኩንታል የስንዴ፣ የበቆሎ፣ የድንች፣ የነጭ ሽንኩርት ሰብል ዘሮችን ለማምረት ተችሏል፡፡ እንዲሁም በአራተኛው ሩብ አመት በበርከሌ 3 ኩንታል የበቆሎ ዘር፣ 5 ኩንታል የቦሎቄ ዘር፤ በራሬ 5 ኩንታል የድንች ዘር እንዲሁም ለዘር አምራች ማህበራት የዘርና ሌሎች ግብኣቶችን ድጋፍ በማድረግ 2040 ኩንታል የድንች ዘር ተመርቶ በምስራቅና በምዕራብ ሐረርጌ ያለውን የዘር እጥረት ችግርን መቀነስ ተችሏል፡፡

ሠንጠረዥ 9 የተሻሻሉ ቴክኖሎጂዎች የዘር ብዜት ስራ

| ተ.ቁ. | የተባዛ የዘር አይነት | የተመረተበት ቦታ | መጠን በኩንታል |
|---|---|---|---|
| 1 | ድንች | በዩኒቨርሲቲው የምርምር ማዕከል | 911 |
| | | በዘር አምራች ማህበራት | 4687 |
| 2 | ማሽላ | በዩኒቨርሲቲው የምርምር ማዕከል | 25 |
| 3 | ስንዴ | በዩኒቨርሲቲው የምርምር ማዕከል | 30 |
| | | በዘር አምራች ማህበራት | 402 |
| 4 | በቆሎ | በዩኒቨርሲቲው የምርምር ማዕከል | 8 |
| | | በዘር አምራች ማህበራት | 89 |
| 5 | ቦሎቄ | በዩኒቨርሲቲው የምርምር ማዕከል | 16 |
| 6 | ነጭ ሽንኩርት | በዩኒቨርሲቲው የምርምር ማዕከል | 0.7 |
| 7 | ለውዝ | በዘር አምራች ማህበራት | 90 |
| | | **ድምር** | **6258.7** |



የዘር ክምችት በከፊል

በተጨማሪም በBENEFIT-ISSD ከ665 ኪ.ግ. በላይ (የማሽላ፣ የስንዴ፣ የጤፍና የቦሎቄ) ምርጥ ዝርያዎች ከምርምር ማዕከላት በማሰባሰብ በኩታ ገጠም የተደራጁ የምዕራብና የምስራቅ ሐረርጌ 1200 አርሶ አደሮች ምርጥ ዘር እንዲያመርቱ ተደርጎ ተሰራጭተዋል፡፡

5. ስለ ቴክኖሎጂ አጠቃቀም ለባለድርሻ አካላት ስልጠና ለመስጠት በተያዘው እቅድ መሠረት የእቅዱን 114% ማከናወን ተችሏል፡፡

ለ36 የልማት ሰራተኞችና የግብርና ኤክስፐርቶች በሐረማያ ወረዳ እንዲሁም ለ66 ነባር ዘር አምራች ማህበራት አባላት ስለ ዘር ጥራት አመራረት ስልጠና ተሰጥቷል፡፡



የዘር አምራች ማህበራትን ለማጠናከር የተሰጠ ስልጠና በከፊል

በአራተኛው ሩብ አመት 85 ለሚሆኑ ከባቢሌ ወረዳ ለተውጣጡ የልማት ሰራተኞች፣ አርሶ አደሮችና የግብርና ኤክስፐርቶች በለውዝ አመራረትና አያያዝ ላይ እንዲሁም 60 (30 ሴትና 30 ወንድ) ለሚሆኑ አርሶ አደሮች በ Dryland Coordination Group(DCG) ፕሮጀክት ድጋፍ የአየር ንብረት ለውጥን መቋቋም የሚችል የድንች አመራረት ላይ ስልጠናዎች ተሰጥተዋል፡፡ በተጨማሪም በዚሁ ሩብ አመት በBENEFIT-ISSD አሳታፊ በሆነ የተለያዩ ሰብሎች (ቦሎቄ፣ማሽላ፣ስንዴ እና ጤፍ) ዝርያ መረጣ እና አመራረት ላይ ከምዕራብ እና ምስራቅ ሀረርጌ ስድስት ወረዳዎች ለተውጣጡ 44 ኤክስፐርቶችና የልማት ሰራተኞች ስልጠና ተሰጥቷል፡፡



የወረዳ ኤክስፐርቶችና የልማት ሰራተኞች ስልጠና በከፊል

6. ለባለድርሻ አካላት የመስክ ቀን ለማዘጋጀት በታቀደው መሠረት የእቅዱን 267% ማከናወን ተችሏል፡፡

በአንደኛው ሩብ አመት የአርሶ አደር፣ የተመራማሪዎቸና የሌሎች ባለድርሻ አካላትን ያሳተፈ የመስክ ቀን ለማዘጋጀት በተያዘው እቅድ መሠረት በዩኒቨርሲቲው ዋናው ግቢ የምርምር ጣቢያዎች ወደ 300 የሚሆኑ ተሳታፊዎች በተገኙበት የምርምር የመስክ ምልከታና ውይይት ተካሂዶ ጥሩ ግብአት ተገኝቷል፡፡



የባለድርሻ አካላት የመስክ ቀን በከፊል

በሁለተኛው ሩብ አመት ደግሞ በጭናቅሰን በግራዋ በጃርሶ በባቢሌና በሐረማያ መልካ ቡባ ተጨማሪ አምስት የመስክ ቀናት ተዘጋጅተው የተለያዩ የልማት አጋሮች በተገኙበት በአሉ የተካሄደ ሲሆን፤ ይህም የምርምር እና ስርጸት፤ የመልካም ተሞክሮ መጋራትና ውጤቶችን ለአራሶ አደሮች ለማሳየት አጋጣሚ ተፈጠሮአል፡፡



የባለድርሻ አካላት የመስክ ቀን በከፊል

በሶስተኛው ሩብ አመት በዋናው ግቢ (በራሬ ምርምር ጣቢያ) የተለያዩ የልማት አጋሮች፣ የልማት ሰራተኞችና ሞዴል አርሶ ደሮች በተገኙበት የመስክ ቀን ተካሂዶ ተጨባጭ የምርምር እና ስርጸት የመልካም ተሞክሮ ማስፋፋት ስራ ተሰርቷል፡፡
በአራተኛው ሩብ አመት ደግሞ Fair Planet ከተባለ የውጪ ድርጅት ጋር በመተባበር 45 ባለድርሻ አካላት የተሳተፉበት የቲማቲም፣ የቃሪያና የሽንኩረት ቴክኖሎጂዎች ላይ የመስክ ቀን ተካሂዶ ተሳታፊዎች ልምድ እንዲቀስሙ ተደርጓል፡፡



በራሬ ምርምር ጣቢያ ከ Fair Planet ጋር የተከናወነ የመስክ ቀን

7. አመታዊ እና ሌሎች የምርምር አውደ ጥናቶችን ለማካሄድ በተያዘው እቅድ መሠረት የእቅዱ 150% ሊካሄድ ተችሏል፡፡

በመጀመሪያው ሩብ አመት "ምርምር፣ ፓሊሲ እና ሚዲያ" በሚል ርእስ በINDEPTH Network፣ በስድስት ዩኒቨርስቲዎች እና በኢትዮጵያ የህብረተሰብ ጤና ማህበር አስተባባሪነት በተካሄደው አገር አቀፍ አውደ ጥናት ከምርምር የሚወጡ ጠቃሚ መረጃዎች በሐገር አቀፍ ሊደግፉ የሚችሉን አቅጣጫ የተመለከተ ሲሆን በሀገሪቱ የሚገኙ ቀርሳን ጨምሮ ስድስቱ የዴሞግራፊክ ክትትልና የጤና ምርምር ማእከላት የተገኘ የጥናት ውጤት በማሳያነት ቀርቧል፡፡



የአገር አቀፉ አውደ ጥናት ተሳታፊዎች

በሁለተኛው ሩብ አመት ValueSeC ከተባለ ፕሮጀክት ጋር በመተባበር በግብርና ምርቶች እሴት ሰንሰለት ዙሪያ አውደ ጥናት ተዘጋጅቶ በዝግጅቱ ላይ ከ100 በላይ ተሳታፊዎች የተገኙ ሲሆን አስራ ስድስ የምርምር ጽሁፎች ቀርበው ውይይት ተካሂዶባቸዋል፡፡


የአውደ ጥናት ተሳታፊዎች በከፊል

በተጨማሪም ከDryland Coordination Group (DCG) ፕሮጀክት ጋር በመተባበር የድንችን ምርታማነት የአየር ለውጥ ተጽዕኖ ባለበት ሁኔታ ውስጥ ማሳደግ በሚቻልበት ዙሪያ አውደ ጥናት የተካሄደ ሲሆን 50 ያህል ተሳታፊዎች በተገኙበት ወደ 10 የምርመር ስራዎች ቀርበው ውይይት ተካሂዶባቸው መልካም ተሞክሮ ተቀምሯል፡፡


የአውደ ጥናቱ ተሳታፊዎች በከፊል

በአራተኛው ሩብ አመት ጽ/ቤቱ በሌሎች ሩብ አመታት በራሱ ካዘጋጃቸው አውደ ጥናቶች በተጨማሪ በሌሎች አካላት የተዘጋጁትን አውደ ጥናቶች በግንባር ቀደምትነት የፋይናንስና ሎጂስቲክስ ድጋፍ አድርጓል፡፡ እነዚህ አውደ ጥናቶች በ"Socio-economic History of Eastern Ethiopia" በሚል ርዕስ ላይ በCSSH የተዘጋጀውን፣ በኢትዮጵያ ሆርቲካልቸር ባለሙያዎች ማህበር የተዘጋጀውን አመታዊ ኮንፍረንስ እንዲሁም በBENEFIT-ISSD የተዘጋጀው የምርጥ ዘር ጥራት ማረጋገጫና የዘር አምራች ክፍሎችን ማዋቀር አስመልክቶ የተዘጋጀውን ያጠቃልላል፡፡

8. የምርምር አውደ ርዕይ ለማዘጋጀት በተያዘው እቅድ መሠረት የእቅዱን 175% ማሳካት ተችሏል፡፡

በአመቱ በደቡብ አፍሪካ በRUFORUM ኮንፍረንስ፣ በሀረር ከተማ በተካሄዱት የብሄር ብሔረሰቦች ቀን አከባበር እና የኢትዮጵያ የህብረተሰብ ጤና አጠባበቅ ማህበር 28ኛው አመታዊ አገር አቀፍ አውደ ጥናት፣ በሐረማያ ዩኒቨርሲቲ ዋናው ግቢ በተካሄዱት የClimate Smart Agriculture and Biodiversity Conservation (CSABC) የካሪኩለም ግምገማ ጉባኤ እና የኢትዮጵያ የሆርቲካልቸር ባለሙያዎች ማህበር ጉባኤ እንዲሁም ጎንደር ከተማ ላይ በተካሄደው የከተሞች ቀን አከባበር ላይ ጽ/ቤቱ የተለያዩ ቴክኖሎጂዎችን አስጎብኝቷል፡፡



የአውደ ርዕይ ተሳትፎ በከፊል

9. የተደራጁ ወጣቶችን የቴክኖሎጂ ተጠቃሚ ለማድረግ በተያዘው እቅድ መሠረት የእቅዱን 166.7% ማከናወን ተችሏል፡፡

በባቴ ዳሞታ ቱታ ከኒሳ ማህበር 15 ወጣቶችን ተጠቃሚ ያደረገ የጠብታ መስኖ ቴክኖሎጂ እና የተለያዩ አትክልት ዝርያዎች ተሰጥተው የወጣቶቹ የገቢያቸው እንዲሻሻል ሆኗል፡፡ በተጨማሪም በሐረማያ ወረዳ በአዴሌ ወልተሀ እና ቢፍቱ ገዳ ቀበሌ ገ/ማህበራት ሁለት በድምሩ 10 የሚሆኑ የተደራጁ ስራ አጥ ወጣቶችን ተጠቃሚ ያደረገ የአትክልት ቴክኖሎጂ (የካሮት፣ ድንች፣ ነጭ ሽንኩርት፣ ሰኳር ድንችና ቀይ ሽንኩርት) ቀርቦላቸዋል፡፡


የተደራጁ ወጣቶችን የቴክኖሎጂ ተጠቃሚ

10. የሴቶችን የቴክኖሎጂ (ሀይል ቆጣቢ ምድጃ፣ዘመናዊ የዶሮ እርባታን) ተጠቃሚታቸውን ለማጎልበት በተደረገው ጥረት መሠረት የእቅዱን 75% ማከናወን ተችሏል፡፡

በሜታ ወረዳ አንድ የሴቶች ማህበር (በድምሩ 70 የሚሆኑ አባላትን የያዘ) የስንዴ፣ የሽምብራ እና የቦሎቄ ቴክኖሎጂዎች እንዲደርሳቸው ተደርጓል፡፡ በተጨማሪም በሜታ፣ በሐረማያ እና በኮምቦልቻ በድምሩ ለ50 ሴት አርሶ አደሮች የተሻሻሉ የወተት ላም እንዲደርሳቸው ተደርጓል፡፡

11. የምርምር ህትመቶችን (አምስት ጆርናሎች፣ አራት ፕሮሲዲንግ፣ መመሪያ ሰነዶች እና መጽሄት) ለማሳተም በተያዘው እቅድ መሠረት የእቅዱን 100% ማሳካት ተችሏል፡፡

የዩኒቨርሲቲውን የ'East African Journal of Sciences' ጆርናል ሁለት ቅጾች እያንዳንዳቸውን በ500 ቅጂ በማሳተም ለተጠቃሚዎች ተሰራጭተዋል፡፡ በሁለተኛው ሩብ አመት ደግሞ 'East African Journal of Health and Biomedical Sciences' የመጀመሪያው እትም ታትሞ ተሰራጭቷል፡፡

በአራተኛው ሩብ አመት 'East African Journal of Sciences አስረኛው ጥራዝ ሁለት ቅጾች እያንዳንዳቸው በ500 ቅጂ ታትመው ተሰራጭተዋል፡፡ በተጨማሪም Haramaya Law Review አራተኛ ጥራዝ በ300 ቅጂ ታትመው ተሰራጭቷል፡፡ እንዲሁም Value Chain Development for Food Security and Pro-poor Development በሚል ርዕስ ላይ የቀረቡ የምርምር ስራዎችን የያዘ የአውደ ጥናት ፕሮሲዲንግ በ300 ቅጂ ታትሞ ተሰራጭቷል፡፡

12. የተለያዩ ሳይንሳዊ የምርምር መጣጥፎችን (articles) በሚገመገሙ (Peer-reviewed) ጆርናሎች እንዲታተሙ የገንዘብ ድጋፍ ለማድረግ በተያዘው እቅድ መሠረት የእቅዱን 107% ማሳካት ተችሏል፡፡

በአንደኛው ሩብ አመት ሶስት ለሚሆኑ የምርምር መጣጥፎች በአለም አቀፍ ጆርናሎች እንዲታተሙ የገንዘብ ድጋር ተደርጎላቸዋል፡፡ በሁለተኛው ሩብ አመት ደግሞ ለአራት የምርምር ጽሁፎች ማሳተሚያ የገንዘብ ድጋፍ ተደርጓል፡፡ እንዲሁም በሶስተኛውና በአራተኛው ሩብ አመት በአጠቃላይ ዘጠኝ የምርምር ጽሁፎች ማሳተሚያ የገንዘብ ድጋፍ ተደርጓል፡፡

የምርምር ህትመት ስራ እና ስርጭትን በተመለከተ በአመቱ የሚከተሉት ስራዎች ተፈጽመዋል፡


- የ33ኛው አመታዊ የምርምር ስራ ውጤት የሆነውን ፕሮሲዲንግ በቲም ሊደሮች፣ በቋንቋ ባለሞያ አስገምግሞ ጥራቱን የጠበቀ የምርምር ስራ ሁኖ እንዲገኝና የመጨረሻ ስራው በህትመት መልክ በየቴሙ በመለየትና በማሳተም ለተመራማሪዎችና ጉዳዩ ለሚመለከታቸው ቢሮች አሰራጨቷል፡፡
- እንደሚታወቀው ወጪን ከመቆጠብ እንጻር የምርምር ቢሮን ዋና ስራዎችን የሚገልጽና አላማውም ለተለያዩ ፕሮገራሞች እንዲውል በማሰብ የማስታወሻ ድብተርን ዲዛን በማድረግ ህትመቱ ተጠናቋል፡፡
- የምርምር ስራን የሚዳስስ የዜና መጽሄት የአጻጻፍ ሂደቱን፣ የግረፊክስ ስራውንና የህትመት አካሄዱን በመከተል ስራው ተጠናቆ ለተለያዩ ቢሮዎች እየተዳረሰ ይገኛል፡፡
- የጠብታ መስኖን ቴክኖሎጂን በጥልቀት በተለያዩ ሚዲያዎች ለማሰወቅ የተቻለ ስሆን፣ በተለይ በኦሮሚያ እና ኢትዮጲያ ቴሌቪዥን ለማስተዋወቅ ተችሏል፡፡
- የ'East African Journal of Sciences'፣ የ'East African Journal of Health and Biomedical Sciences' እና የ'East African Journal of Social Sciences and Humanities' online ISSN መለያ ተገኝቷል፡፡

ሠንጠረዥ 10 የህትመት አይነትና ብዛት ማጠቃለያ

| ተ.ቁ | የህትመቱ አይነት | የህትመት ብዛት | አስተያየት |
|---|---|---|---|
| 1. | የ33ኛው አመታዊ ፕሮሲዲንግ (Theme I) | 300 | ለተለያዩ ክፍሎች ተሰራጭቷል |
| 2. | የ33ኛው አመታዊ ፕሮሲዲንግ (Theme II) | 300 | ለተለያዩ ክፍሎች ተሰራጭቷል |
| 3. | የ33ኛው አመታዊ ፕሮሲዲንግ (Theme III, IV and V) | 300 | የመጻሀፉ የገጽ ብዛትን ከግንዛቤ በማድረግ አንድ ላይ የታተመ ሲሆን በውስጡ ግን በየቴሙ ተከፋፍሏል፡ |
| 4. | የምርመር የዜና መጽሄት | 2000 | ለተለያዩ ክፍሎች ተሰራጭቷል |
| 5. | የምርምር ጽ/ቤቱን መረጃ የያዘ የማታወሻ ድብተር ተዘጋጅቶ ታትሟል | 2000 | ለተለያዩ ፕሮግራሞች እንዲውል የታሰበ |
| 6. | East African Journal of Health and Biomedical Sciences | 500 | ለተለያዩ ክፍሎች ተሰራጭቷል |
| 7. | East African Journal of Social Sciences and Humanities | 500 | ለተለያዩ ክፍሎች ተሰራጭቷል |
| 8. | East African Journal of Sciences Vol. 10 Issue 1 | 500 | ለተለያዩ ክፍሎች ተሰራጭቷል |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 9. | East African Journal of Sciences Vol. 10 Issue 2 | 500 | ለተለያዩ ክፍሎች ተሰራጭቷል |
| 10. | Value Chain Development for Food Security and Pro-poor Development Proceeding | 300 | ለተለያዩ ክፍሎች ተሰራጭቷል |
| 11. | Haramaya Law Review Vol. 4 Issue 1 | 300 | ለተለያዩ ክፍሎች ተሰራጭቷል |

ከዚህ በተጨማሪ ተመራማሪዎች በተለያዩ አገራዊና አለም አቀፍ የምርምር ድርሳናት ላይ ያሳተሙትን የምርምር ስራ ለመመዝገብ በተደረገው ጥረት በአመቱ በድምሩ 483 የምርምር ጽሁፎች የተመዘገቡ ሲሆን በኮሌጅ እና በምርምር ትኩረት አቅጣጫ በሚከተለው ግራፍ ተከፋፍሎ ተቀምታል፡፡




የአመቱ በተለያዩ አገራዊና አለም አቀፍ የምርምር ድርሳናት ላይ የታተሙና የተመዘገቡ ጽሁፎች በኮሌጅ እና በምርምር ትኩረት አቅጣጫ

## እይታ 2፡ የፋይናንስ/በጀት እይታ

### ግብ 5፡ የምርመር ድጋፍ ምንጮችን ማሳደግ

**ውጤት፡ ያደገ የምርመር ድጋፍ ምንጭ**

**ዋና ዋና ተግባራት፡**

1. ከኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት ጋር እና ሌሎች በሀገር ውስጥ ካሉ ድርጅቶች የምርምር ድጋፍ በተያዘው እቅድ መሠረት የእቅዱን 100% ማከናወን የተቻለ ሲሆን በጥረቱ 1.2 ሚሊዮን ብር ተገኝቷል፡፡

2. ከተለያዩ አገር አቀፍ እና አለም አቀፍ ድርጅቶች የምርምር በጀት ለማግኘት በተያዘው እቅድ መሠረት የእቅዱን 125% ማከናወን ተጭሏል፡፡

   በአመቱ ከውጭ ድርጅቶች በትብብር የሚሰሩ 28 ፕሮጀክቶች የተመዘገቡ ሲሆን ከእነዚህ ፕሮጀክቶች በጠቅላላ 21,031,405 ዶላር ድጋፍ ለማግኘት ተችሏል፡፡ እነዚህ ፕሮጀክቶች በዚህ በጀት አመት 5,715,727 ዶላር ተጠቅመዋል፡፡

ሠንጠረዥ 11 ፕሮጀክቶቹ የሚያተኩሩባቸው የጥናት መስኮች

| Field of Study | Projects | Total Budget in US Dollar | Current fiscal year budget |
|---|---|---|---|
| **Health** | 6 | 4,090,420 | 2,035,548 |
| **Agriculture** | 18 | 10,356,821 | 2,199,136 |
| **Law related** | 3 | 6,234,164 | 1,306,043 |
| **Technology** | 1 | 350,000 | 175,000 |
| **Total** | **28** | **21,031,405** | **5,715,727** |




የድጋፍ ሰጪ ድርጅቶች በከፊል

እንዲሁም ከአዲስ አበባ እና Vienna ዩኒቨርሲቲዎች ጋር በአጋርነት ለመስራት የጋራ የምርምር ፕሮጀክት ተቀርጾ የፕሮጀክቱ ንድፈ ሀሳብ ለኦስትሪያ መንግስት ቀርቦ ውጤቱ እየተጠበቀ ይገኛል፡፡ በተጨማሪም ከWisconsin Madisson University ጋር በአጋርነት ለመስራት በዩኒቨርሲቲው ተወካዮችና ከሐረማያ ዩኒቨርሲቲ ከተውጣጡ አንጋፋ ተመራማሪዎች ጋር ሰፋ ያለ ውይይት ተደርጎ ትብብር የሚደረግባቸው መስኮች ከተለዩ በኋላ ዩኒቨርሲቲዎቹ የመግባቢያ ሰነድ ተፈራርመዋል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ ከFlorida University ጋር በጋራ ለመስራት ከስምምነት ተደርሷል፡፡



የሐረማያ ዩኒቨርሲቲና የWisconsin Madisson University ተወካዮች

ከVan Hall Larenstein University of Applied Sciences ጋር በመተባበር የወተት ምርት እሴት ሰንሰለት ዙሪያ የጋራ ፕሮጀክት በመቅረጽ ለNOW/CCAFS የገንዘብ ድጋፍ ንድፈ ሀሳብ ተልኮ ውሳኔ እየተጠበቀ ይገኛል፡፡

በተጨማሪም የምርምር ጉዳዮች ጽ/ቤት ተመራማሪዎች የፕሮጀክት ንድፈ ሀሳቦችን እንዲቀርጹ ድጋፍ በማድረግ "Improving Quality and Relevance of University Entrepreneurship Education in African Universities" በሚል ርዕስ ላይ ለSPHEIR/DFID ድጋፍ፣ "Intra-Africa University Collaboration to Strengthen Engineering Education" በሚል ርዕስ ላይ ለEU-Intra-Africa Mobility Scheme ድጋፍ እና "Manufacturing Engineering" በሚል ርዕስ ላይ ለErasmus Plus ድጋፍ ለመጠየቅ ንድፈ ሀሳቦች ተቀርጸው ተልከዋል፡፡ እንዲሁም የነበረውን አጋርነት በማጠናከር ከUniversity College Cork of Ireland ጋር በመተባበር "AgriDiet-Choice" በሚል ርዕስ ላይ ንድፈ ሀሳብ ተቀርጾ ለUK Aid እና Bill & Melinda Gates Foundation ተልኳል፡፡

እንዲሁም ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ የመጣውን የዩኒቨርሲቲውን የውጪ ፕሮጀክቶች ድጋፍ ተከትሎ በመረጃ አለመጠናቀር ምክንያት ዩኒቨርሲቲው በአጋርነት እየሰራቸው ያሉትን ፕሮጀክቶች ማውቅና ማሳወቅ ባለመቻሉ ይህንኑ ችግር ለመቅረፍ የምርምር ጉዳዮች ጽ/ቤት የውጪ ፕሮጀክቶች አስተዳደር መመሪያ አዘጋጅቶና በተለያየ ደረጃ አስገምግሞ በዩኒቨርሲቲው ሴኔት አጸድቋል፡፡

## ግብ 6፡ የሐብት አጠቃቀምን ማሻሻል

**ውጤት**1፡ የተሳለጠ የሀብት አጠቃቀም/ጥቅም ላይ የዋለ ሀብት

**ዋና ዋና ተግባራት፡**

1. በከፍተኛ ወጪ ከሌሎች ቦታዎች የሚመጣውን የእንስሳት መኖ በአካባቢው በማምረት ወጪን ለመቀነስ በታቀደው መሠረት የእቅዱን 100% ማከናወን ተችሏል፡፡

   በዩኒቨርስቲው ውስጥ በተለያዩ ቦታዎች የከብት መኖን በወቅቱ በማጨድና፣ በማሰባሰብ በማጠራቀም በድምሩ 250 ሺ ብር መኖን ለመግዛት ይወጣ የነበረን በጀት ለማዳን ተችሏል፡፡ በሶስተኛው ሩብ ዓመትም ግምቱ 50ሺ ብር የሚሆን በተለያዩ ቦታዎች የከብት መኖን እንዲመረቱ በማድረግ ወጪን ለመቀነስ ተችሏል፡፡ በአጠቃላይ በአመቱ 350ሺ ብር ወጪ ለማዳን ተችሏል፡፡

2. የበጀት አጠቃቀምን ለማሻሻል በታቀደው መሠረት የእቅዱን 100% ማከናወን ተችሏል፡፡ በአመቱ በምርምር ጽ/ቤቱ የተመደቡ በጀቶችን አጠቃቀም በመከታተል በጽ/ቤቱ የታቀዱ ዋና ዋና ተግባራት የበጀት እጥረት ሳይኖር ተከናውነዋል፡፡

3. የምርምር ፈንዶችን በአግባቡ ጥቅም ላይ መዋላቸውን ለመከታተልና ለማከናወን በተያዘው እቅድ መሠረት የእቅዱን 100% ማከናወን ተችሏል፡፡ በየዳይሬክቶሬቶቹ በየወሩ የመገማገሚያ መድረክ በማዘጋጀት እና በሩብ አመት አንዴ በምርምር ጉዳዮች ጽ/ቤት ደረጃ ግምገማ በማድረግና ዋና ዋና ችግሮችን ነቅሶ በማውጣት የማክሰሚያ ስልቶች ተነድፈዋል፡፡ በአጠቃላይ በአመቱ አራት የውይይት መድረኮች የተዘጋጁ ሲሆን ጥሩ ግብአትም ተገኝቶበታል፡፡

4. የመስክ ጉብኝትና ክትትል ለማድረግ በተያዘው እቅድ መሠረት የእቅዱን 100% ማከናወን ተችሏል፡፡ በተለያዩ ወረዳዎች የተሰሩ የቴክኖሎጂ ሽግግር ስራዎችን እና የምርምር ጣቢያዎችን ስራ በተያዘላቸው እቅድ መሠረት መከናወናቸውን ለመከታተል በየሩብ አመቱ በጽህፈት ቤት ደረጃ አንድ ጊዜ በድምሩ አራት የመስክ ጉብኝቶች ተደርገዋል፡፡ በነዚህ ጉብኝቶች መልካም ተሞክሮዎችንና ተግዳሮቶችን ለመለየት የተቻለ ሲሆን ለተግዳሮቶቹ የመፍትሄ ሃሳብ ማስቀመጥ ተችሏል፡፡



በድሬዳዋ ምርምር ጣቢያ የስራ ጉብኝት

5. የምርምር ቴክኖሎጂዎችና ተረፈ ምርቶችን የገቢ ምንጭ እንዲሆኑ ለማስቻል በተያዘው እቅድ መሠረት የእቅዱን 95% ማከናወን ተችሏል፡፡ በአመቱ ከብርቱኳን ምርትና ችግኝ፣ ከበግ፣ ከፍየል፣ ከመንደሪን ችግኝ፣ ከስኳር ድንች፣ ከጥቅል ጎመን፣ ከቃሪያ፣ ከድንች፣ ከሽንኩርት፣ ከቲማቲም እና ከመሳሰሉት ከምርምር ውጤቶችና ተረፈ ምርቶች ሽያጭ 5.714 ሚሊየን ብር ገቢ ተገኝቷል፡፡

6. አገልግሎት የማይሰጡ ንብረቶችን ስራ ላይ እንዲውሉ ለማስቻል በተያዘው እቅድ መሠረት የእቅዱን 100% ማከናወን ተችሏል፡፡ ከዚህ በፊት ለምርምር ስራ ተገዝተው ለረጅም ጊዜ ጥቅም ላይ ሳይውሉ የቆዩ የተለያዩ የጠብታ መስኖ ግብአቶችን በመጠቀም በሐረማያ ዙሪያ ለሚገኙ ሶስት ቀበሌዎች ውስጥ በእያንዳንዳቸው 0.5 ሄክታር መሬት እንዲለማ ተደርጓል፡፡ በአጠቃላይ በአመቱ አገልግሎት የማይሰጡ ንብረቶችን መልሶ ጥቅም ላይ በማዋል በግምት 300ሺ.ህ ብር ለማዳን ተችሏል፡፡

## እይታ 3፡ የውስጥ አሰራር ሂደት እይታ

### ግብ 7፡ የስራ ሂደቶችን ቅልጥፍናና ስልጠት ማሳደግ

**ውጤት፡** ያደገ እና የተሳለጠ የስራ ሂደቶች

**ዋና ዋና ተግባራት፡**

1. አቅም ለመገንባትና ክትትል ለማድረግ በተያዘው እቅድ መሠረት የእቅዱን 100% ማከናወን ተችሏል፡፡ በየደረጃው የሚገኙ የአሰራር ጥራት ክፍተቶች እና መልካም ጅምሮችን በመለየት፣ በመገምገም እና በመከታተል የአቅም ግንባታ ስራ ተሰርቷል፡፡

2. መልካም አስተዳደርን ለማስፈን የልማት ሰራዊት (የምርምር ቡድኖች) ለመገንባት፣ ለመከታተልና ለመደገፍ በታቀደው መሠረት የእቅዱን 195% ማከናወን ተችሏል፡፡

   በምርምር ፋሲሊቲዎች ማኔጅመንት 20፣ በምርመር ቡድኖችና አጋርነት 22 እና በምርምር ስርጸትና ህትመት 2 በድምሩ 44 የልማት ሰራዊት ተገንብቷል፡፡ በዚሁ መሰረት በአስተባባሪዎች ደረጃ በየሳምንቱ፣ በዳይሬክቶሬት ደረጃ በወር እና በምርምር ጽ/ቤት ደረጃ በየሩብ አመቱ ውይይቶች ተካሂደው ለተከሰቱ ችግሮች የመፍትሄ አቅጣጫ ተቀምጠላቸዋል፡፡

3. የመስክ ጉብኝት፣ ክትትል፣ ግምገማና ድጋፍ ለማድረግ በተያዘው እቅድ መሠረት የእቅዱን 100% ማከናወን ተችሏል፡፡ በዳይሬክተሮች ደረጃ በየወሩ፣ በምርምር አቅጣጫ መሪዎች ደግሞ በየሩብ አመቱ አንድ ግዜ በስራቸው የሚገኙትን የምርምር ፕሮጀክቶች በሚሰሩበት ቦታ በመገኘት አመራርና ድጋፍ ተሰጥቷል፡፡

### ግብ 8፡ የአመራር ብቃትን፡የስራ አቅምንና ተነሳሽነትን ማሳደግ

**ውጤት፡** ያደገ የአመራር ብቃት እና ተነሳሽነት

**ዋና ዋና ተግባራት፡**

1. የስራ ላይ ስልጠና ለመስጠት (on job Training) በታቀደው መሠረት የእቅዱን 100% ማከናወን ተችሏል፡፡ የሰራተኞችን የስራ አሰራር እና አመለካከትን ለማሻሻል ለ40 ሰራተኞች የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራ ተሰርቷል፡፡ በዚሁ መሠረት በአመቱ በአንድ ለአምስት አደረጃጀትና አሰራር፣ በስራ ሂደት ቅልጥፍናና ስልጠት እና በተጓዳኝ ጉዳዮች ዙሪያ ስልጠና ተሰጥቶ የስራ አፈጻጸምን ለማሻሻል ተችሏል፡፡

2. የስራ አመራርና የስራ አፈጻጸም ሪፖርት አቀራረብ ላይ ስልጠና ለመስጠት በተያዘው እቅድ መሠረት የእቅዱን 91% ማከናወን ተችሏል፡፡ በዚሁ መሠረት 20 ለሚሆኑ የምርምር ጣቢያ አስተባባሪዎች፣ ሱፐርቫይዘሮችና የመስክ ስራ አስተባባሪዎች ስልጠና ተሰጥቷል፡፡



የስራ አመራርና የስራ አፈጻጸም ሪፖርት አቀራረብ ስልጠና

3. በስራ ምዘና ከፍተኛ ውጤት ላስመዘገቡ ሽልማት ለመስጠት በተያዘው እቅድ መሠረት የእቅዱን 90% ማከናወን ተችሏል፡፡ ለ9 የምርምር ጣቢያ አስተባባሪዎች እና ጥበቃ አስተባባሪዎች ሽልማት ተበርክቶላቸዋል፡፡ በተጨማሪም በሽልማት ስነ-ስርአቱ ላይ የምርምር ም/ፕሬዝደንት በተገኙበት ወደ ፊት ሊተኮርባቸው በሚገቡ ጉዳዮች ላይ ሰፋ ያለ ውይይትና በድሬዳዋ የዩኒቨርሲቲው የምርምር ማዕከል የመስክ ምልከታ ተካሂዷል፡፡



በስራ ምዘና ከፍተኛ ውጤት ያስመዘገቡ ተሸላሚዎች



በድሬዳዋ ምርምር ጣቢያ የተደረገ ውይይት በከፊል

4. በአመቱ የልምድ ልውውጥ ጉብኝት ለማድረግና መልካም ተሞክሮዎችን ለመቀመር በታቀደው መሠረት የእቅዱን 117% ማከናወን ተችሏል፡፡ በዶሮ እርባታ ቴክኖሎጂ ላይ ከደብረ ዘይት ግብርና ምርምር ጋር በመቀናጀት በተሻሻሉ የዶሮ ዝርያዎች ላይ በአርሶ አደር ደረጃ እና በምርምር ማዕከል የተሰሩ ስራዎችን በመጎብኘት የልምድ ልውውጥ ተደርጓል፡፡ በተጨማሪም አምስት የምርምር መጽሄት አቀናባሪዎች ልምድ ያገኙ ዘንድ የተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎችን በመጎብኘት መልካም ተሞክሮዎችን መቅሰም ችለዋል::

ሶስት አባላት የያዘ ቡድን በሆለታና በስምጥ ሸለቆ አካባቢዎች የሚገኙ የምርምር ቦታዎችን የጎበኙ ሲሆን የመስኖ ውሀ አጠቃቀም፣ የላብራቶሪ አደራጃጀትና የምርምር ስራ ሂደት ዙሪያ ልምድ የቀሰሙ ሲሆን በተጨማሪም የኢትዮጵያ ሳይንስ እና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴርን አደረጃጀት፣ አሰራርና የምርመርና የኢንኩቤሽን ማዕከልን ጎብኝተዋል፡፡

በተጨማሪም በኢነርጂ ኢንጅነሪንግ እና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ስር የሚገኙ ተመራማሪዎች በቆጮ ምርት የሚታወቁትን የጉራጌ እና የወላይታ ዞኖችን በመጎብኘት ጠቃሚ የሆኑ ተሞክሮችን፣ አሰራሮችን፣ ማቀነባበሪያዎችን ልምድ ቀስመዋል፡፡ ከዚሁ የምርምር የትኩረት መስክ የተውጣጡ 6 አባላት ያሉት የምርምር ቡድን በአዲስ አበባ የሚገኙ የምርምርና ኢንዱስትሪ ተቋማትን፣ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚንስቴር (Ministry of Science and Technology)፣ የኢትዮጵያ የጨርቃ ጨርቅ ኢንዱስትሪ ማበልፀያ (Ethiopian

Textile Industry Development Institute) እና የኢትዮጵያ ቆዳ ኢንዱስትሪ ማበልፀጊያ (Ethiopian Leather Industry Development Institute) ተቋማትን በመጎብኘት በጋራ ሊሰራ የሚቻልበትን ሁኔታ ለመፍጠር ተችሏል፡፡



የጨርቃ ጨርቅ እና የቆዳ ማበልፀጊያ ኢንዱስትሪዎች ጉብኝት

እንዲሁም ከሌሎች ዩኒቨርሲቲዎችና መንግስታዊና መንግሰታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ለልምድ ልውውጥ ለመጡ አካላት ጽ/ቤቱ አስፈላጊውን ልምድና መልካም ተሞክሮ በማካፍል የዩኒቨርሲቲውን መልካም ገጽታ ለመገንባት ተችሏል፡፡

5. ስልጠና ለመስጠት በተያዘው እቅድ መሠረት የእቅዱን 51.4% ብቻ ማከናወን ተችሏል፡፡ በአራት የምርምር ትኩረት መስክ መሪዎች አስተባባሪነት ለ120 ተመራማሪዎች እንዲሁም በቫሌዩሴክ ፕሮጀክት ድጋፍ ለ33 የድህረ ምረቃ ተማሪዎች ስልጠና ተሰጥቷል፡፡ ከእቅዱ በታች ስራዎች ሊተገበሩ የቻሉት አንዳንድ የትኩረት መስክ አስተባባሪዎች (ምሳሌ፡- የትኩረት መስክ አንድ አስተባባሪ) በእቅዳቸው መሠረት ተከታትለው የማስፈጸም ውስንነት ስለታየባቸው ነው፡፡

በአመቱ የተሰጡት ስልጠናዎች ትኩረት በሚከተሉት ዋና ዋና ርዕሶች ላይ ያተኮሩ ነበሩ፡- የሳይንሳዊ መጣጥፍ (Paper) አዘገጃጀትና የውጤት አቀራረብ፣ በንድፈ ሀሳብ አፃፃፍ (Writing Research Proposals)፣ በሪፖርት አፃፃፍ (Writing Scientific Manuscripts)፣ የጋራ ፕሮጀክት ንድፈ ሀሳብ ዝግጅት (Writing Collaborative Project Proposals) እና ፕሮጀክት መምራት (Project management)፣ በዳታ ማኔጅመንትና ትንተና፣ በGIS and Remote Sensing እና በMatLab Softare፡፡

በተጨማሪም የቀርሳ ዴሞግራፊክ ክትትልና የጤና ምርምር ማዕከል የመረጃ አሰባሰብ ስርአት ወደ ዲጂታል ለመቀየር ቀጥታ ግንኙነት ያላቸውን 23 ሰራተኞች በታብሌት አጠቃቀም እና በታብሌት መረጃ አሰባሰብ ላይ ስልጠና ተሰጥቷል፡፡



ስልጠናዎች በክፊል

እንዲሁም ከማህበረተሰቡ በቀጥታ በቀረበ ከአየር ንብረት ለውጥ ጋር ተያይዞ የተከሰቱ ተላላፊ በሽታዎች ቁጥጥርና ክትትል ዙሪያ ከግልና ከመንግስት የጤና ተቋማት ለተውጣጡ 46 ባለሙያዎች ስልጠና ተሰጥቷል፡፡

## እይታ 4፡ የመማማርና የእድገት እይታ


### ግብ 9፡ የምርምር ፋሲሊቲዎችን ማስፋፋትና ማዘመን

**ውጤት**፡ የተስፋፉና የዘመኑ የምርምር ፋሲሊቲዎች

**ዋና ዋና ተግባራት፡**

1. የምርምር ጣቢያዎችን የይዞታ ማረጋገጫ ለማሰራት በተያዘው እቅድ መሠረት የእቅዱን 200% ማከናወን ተችሏል፡፡

   ለባቢሌ (ለዋናው፣ ለበርከሌ፣ ለግመል ምርምር እና ለጣቢያው ቢሮ) የምርምር ጣቢያ፣ ለግራዋ (የአፕልና አዝርዕት ምርምር ንዑስ ጣቢያዎች) ምርምር ጣቢያ፣ ለፈዲስ ምርምር ጣቢያ፣ ለሂርና ምርምር ጣቢያ የባለቤትነት ማረጋገጫ ካርታ ለማግኘት ተችሏል፡፡ በአጠቃላይ ካሉት የምርምር ጣቢያዎች ውስጥ ያልወጣለት የድሬዳዋ የዩኒቨርሲቲው የምርምር ጣቢያ ብቻ ሲሆን በዚህ አመት ከተያዘው እቅድ አንጻር 200% ተከናውኗል፡፡ በድሬዳዋ ለሚገኘው ጣቢያም የባለቤትነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለማውጣት ከፍተኛ ጥረት እየተደረገ ነው፡፡




የምርምር ጣቢያዎች የባለቤትነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት በከፊል

2. በድሬዳዋ የምርምር ጣቢያ ሁለት ክፍል ቢሮ ለመስራትና ለማጠናቀቅ በተያዘው እቅድ መሠረት የቢሮ ስራው ተጠናቆ በማዕከሉ የነበረውን የቢሮ እጥረት ለመቅረፍ የተቻለ ሲሆን በዚህ ረገድ የእቅዱን 100% ማሳካት ተችሏል፡፡




በድሬዳዋ የምርምር ጣቢያ የተሰራው ቢሮ ሲጎበኝ

3. በጉራዋ የምርምር ጣቢያ የውሃ ቦታዎችን ለመለየትና ለማጎልበት በተያዘው እቅድ መሠረት ቦታዎቹን የመለየት ስራ ተሰርቶ ከእቅዱ 94% ማከናወን የተቻለ ሲሆን የማጎልበቱ ስራ በሚቀጥለው የበጀት አመት ይከናወናል፡፡

4. በኤረር በርከሌ ለቆላ ፍራፍሬ እና አትክልት ምርምር የሚያገለግል አዲስ የምርምር ጣቢያ ለማቋቋም በተያዘው እቅድ መሠረት 50 ሄክታር የሚሆን ቦታ በመረከብና በማሳረስ የዘር ብዜት ስራ የተሰራበት ሲሆን በቀጣይ ደግሞ የተለያዩ የምርምር ስራዎችን በአግባቡ ለይቶ ለማወቅ ያስችል ዘንድ የአፈር ጥናት ስራ፣ የውሃ አቅም የመለየት ጥናት እና የአጠቃላይ የቦታ መከፋፈልና ክለላ ስራ ተጠናቆ የእቅዱን 100% ማሳካት ተችሏል፡፡ ይህንኑ ተከትሎ ሁሉን አቀፍ የምርመር እና የዘር ማባዛት ስራ ተጀምሯል፡፡


የተመራማሪዎች ቡድን የምርምር ጣቢያውን ጎብኝተው ውይይት ሲያደርጉ



የበርከሌ ምርምር ጣቢያ ክፍፍል ፕላን

በበርከሌ የምርምር ጣቢያ የፍራፍሬ ምርምር አስጀምሮ በአገር አቀፍ ደረጃ የልቀት ማዕከል ሊሆን ወደሚችልበት ደረጃ ለማድረስ የፍራፍሬ አይነቶችን አደራጅቶ ለመጀመር ታሰቦ በዚሁ አመት ወደ 38 የሚሆኑ የማንጎ ዝርያዎች ከምስራቅ ሐረርጌና ከተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች ተሰብስበው ችግኝ የማፍላት ስራ ተጀምሯል፡፡


የተሰበሰቡ የማንጎ ዝርያዎች በከፊል

5. የምርምር ጣቢያዎችንና ስራዎችን የሚያስተዋውቁ ዘጋቢ ፊልሞችና ጽሁፎችን ለማሰራት በተያዘው እቅድ መሠረት የእቅዱን 100% ማከናወን ተችሏል፡፡ ከተዘጋጁት ሁለት ዘጋቢ ፊልሞች መካከል አንዱ (ከማህበረሰብ ተሳትፎና ኢንተፕራይዝ ልማት ጽ/ቤት ጋር በመተባበር የተዘጋጀ) በኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮረፖሬሽን የተላለፍ ሲሆን በዩኒቨርሲቲው ባለሙያዎች የተሰራው ሁለተኛው ዘጋቢ ፊልም የእርምት ስራዎች ተጠናቀው ለማህበረሰቡ ይቀርባል፡፡

**ክፍል 4. *ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ መፍህቴዎች***

- *ግዢዎች በታቀደላቸው የጊዜ ገደብ አለመፈፀምና አንዳንድ እቃዎችን ገበያ ላይ አለማግኘት(ኬሚካል)፣*
- *ለምርምር ስራ ይረዳ ዘንደ ከአጋር አካላት የሚተላለፍ በጀት በወቅቱ ለስራ ዝግጁ ያለመሆን፣*
- *በምርምር ፋይናንስ ስር በቂ ፋይናንስ በቋት ያለመያዝና ያለውንም በቶሎ አወራርዶ ተጨማሪ በወቅቱ አለማዘጋጀት፣*
- *የተሽከርካሪ መኪኖች እጥረት፣*
- *በድሬዳዋ የሚገኘው የምርምር ጣቢያ ከድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ ጋር ያለው የይገባኛል ውዝግብ አለመቋጨቱ፣*
- *ተመራማሪዎች በወቅቱ የሰሩትን ስራ ሪፖርት በአግባቡና ጥንቃቄ በተሞላበት ሁኔታ አለማቅረብ፣*
- *ተመራማሪዎች ለምርምር ስራቸው ትኩረት አለመስጠት፣*

*በአጠቃላይ ለተፈጠሩ ችግሮች የምርምር ጉዳዮች ም/ፕሬዚዳንት ጽ/ቤት በስሩ ያሉ ዳይሬክተሮች እንዲሁም የምርምር ትኩረት መስክ መሪዎች የታቀዱት ተግባራት በእቅዱ መሠረት ስለመሰራታቸውና መከናወናቸው ስርዓት ዘርግቶ (በሪፖርቶች፣ በውይይት መድረኮች፣ በመስክ ጉብኝቶች፤ በግምገማዎችና ሌሎች አስፈላጊ ዘዴዎች በመቀመር) ተከታትሎ፣ ድጋፍ በማድረግና ግብረ-መልስ በመስጠት ያገጠሙትን ችግሮች በመቋቋም የታቀዱ ስራዎችን ለማከናወን ተችሏል፡፡*

## ክፍል 5፡ አባሪ

በምርምር ጉዳዮች ም/ፕሬዚደንት ጽ/ቤት ስር ለ2009ዓ.ም. የአራተኛው ሩብ አመትና የአመቱ የስራ ክንዉን

| ዕይታ | የተቋሙ ስትራቴጂካዊ ግቦች | ከስ/ግብና ከተግባር የሚጠበቅ ውጤት | በሥራ ክፍሉ ደረጃ ተመንዝረው የተቀመጡ ስትራቴጂያዊ ግቦች | ስትራቴጂካዊ ግቡን ለማሳካት የሚፈፀሙ አበይት ተግባራት | የግብና የተግባር ክብደት (%) | መለኪያ | መነሻ | የዓመቱ | የ4ኛ ሩብ ዓመት አፈጻጻም | | | የአመቱ አጠቃላይ የስራ አፈጻጸም | | | የአፈጻጸም ዉጤት | ማብራሪያ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | | | ዕቅድ | ክንዉን | ክንዉን (%) | ዕቅድ | ክንዉን | ክንዉን (%) | | |
| የተገልጋይ/ ደንበኛ/ ባለድርሻ ዕይታ | | | | | 63 % | 40 | | | | | | | | | | |
| | የደንበኛውን/ባለድርሻ አካላት እርካታና ተሳትፎ ማሳደግ | ያደገ የደንበኞች/ባለደርሻ አካላት እርካታና ተሳትፎ | የተገልጋዩን እርካታ ማሳደግ | የምርምር ንድፈ ሀሳቦችን ጥሪ በወቅቱ ማውጣት | 1.0 % | በግዜ ሰሌዳ | 1 | 1 | 1 | 1 | 100 | 1 | 1 | 100 | | |
| | | | | የምርምር ንድፈ ሀሳቦችን አሳታፊ በሆነ መልኩ ማስገምገምና መምረጥ | 2.0 % | የተሳተፉ የምርምር የቡድን አባላት | 45 | 110 | 55 | 55 | 100 | 110 | 141 | 128 | | |
| | | | | ፍላጎት ተኮር የቴክኖሎጂ ሽግግር ስራን ማከናወን | 5.0 % | የቴክኖሎጂ ብዛት | 30 | 42 | 2 | 6 | 300 | 42 | 36 | 86 | | |
| | | | | የምርምር ፋሲሊቲዎን በወቅቱ ማቅረብ | 3.0 % | % | 85 | 85 | 85 | 85 | 100 | 85 | 85 | 100 | | |
| | | | የተመራማሪዎችን ተሳትፎ ማሳደግ | የምርምር ትኩረት መሪዎች እና የተመራማሪዎችን በምርምር ፋሲሊቲዎች ማስፋፋት ሂደት ዉስጥ እንዲሳተፉ ማድረግ | 4.0 % | የውይይት መድረክ | 4 | 4 | 1 | 2 | 200 | 4 | 5 | 125 | | |
| | | | | የሴቶችን የልማት ተሳታፊነትና ተጠቃሚነት ማጎልበት | | ተሳታፊዎች በመቶኛ | 10 | 10 | 10 | 10 | 100 | 10 | 10 | 100 | | |

| | | | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | 15.0% | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | | | |
| | የምርምር አጋርነትንና ትስስርን ማሳደግ | ያደገ የምርምር አጋርነትንና ትስስር | የምርምር ስራዎችን ከአጋር አካላት ጋር በመተባበር መንደፍ፣ መስራትና መገምገም | ምርምር የሚሹ ችግሮችን ከባለድርሻ አካላት ጋር መለየት፣ ንድፈ ሀሳብ መቅረጽ | 2.0 % | የንድፈ ሀሳብ ብዛት | 1 | 6 | 1 | 1 | 100 | 6 | 6 | 100 | | |
| | | | | ከኢንደስትሪዎች ጋር የምርምር ትብብር መፍጠር | 1.0 % | ቁጥር | 2 | 6 | 1 | | 66.7 | 5 | 4 | 80 | | |
| | | | | በስድስቱ የምርምር ትኩረት መስኮች ትኩረት የሚሹ የምርመር ፍላጎቶችን ዳሰሳ ጥናት ማካሄድ | 1.0 % | ቁጥር | 1 | 6 | 3 | 2 | 66.7 | 5 | 3 | 60 | | |
| | | | የምርምር ፋሲሊቲዎችን ከአጋር አካላት ጋር በመተባበር ማስፋፋት እና ማዘመን | ከባለድርሻ አካላት ጋር ለስርጸት የሚሆኑ ቴክኖሎጂዎችን (የስኳር ድንች፣ የፍየሎችና የበጎች) ማዘጋጀትና እንዲሰራጩ ማድረግ | 3% | የቴክኖ ሎጂ ቁጥር | 3 | 3 | 1 | 3 | 300 | 3 | 7 | 233 | | |
| | | | | | 7% | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | | | |
| | ፍላጎት ተኮር የምርምር ውጤቶችን ማሳደግ | የደገ ፍላጎት ተኮር የምርመር ውጤቶች | ፍላጎት ተኮር ምርምሮችን መከታተል፣ መደገፍና ማጠናቀቅ | በ “Productivity, Environmental Sustainability for Food Secuity and Poverty alliviation” የምርምር ትኩረት አቅጣጫ ስር ምርምሮችን ማካሄድ፣ መከታተልና መደገፍ | 5.0 % | ቁጥር | 150 | 194 | 194 | 194 | 100 | 194 | 194 | 194 | 100 | |

| | | | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | በ “Human Health, Nutrition and Welfare” የምርምር ትኩረት አቅጣጫ ስር ምርምሮችን ማካሄድ፣ መከታተልና መደገፍ | 3.0 % | ቁጥር | 30 | 75 | 75 | 75 | 100 | 75 | 75 | 75 | 100 | |
| | | | | በ “Energy, Engineering and Information Technologies” የምርምር ትኩረት አቅጣጫ ስር ምርምሮችን ማካሄድ፣ መከታተልና መደገፍ | 3.0 % | ቁጥር | 15 | 30 | 30 | 30 | 100 | 30 | 30 | 100 | | |
| | | | | በ “Human and Social Development” የምርምር ትኩረት አቅጣጫ ስር ምርምሮችን ማካሄድ፣ መከታተልና መደገፍ | 2.0 % | ቁጥር | 17 | 27 | 27 | 27 | 100 | 27 | 27 | 100 | | |
| | | | | በ “Institutions, Innovations Systems, and Economic Development” የምርምር ትኩረት አቅጣጫ ስር ምርምሮችን ማካሄድ፣ መከታተልና መደገፍ | 3.0 % | ቁጥር | 13 | 30 | 30 | 30 | 100 | 30 | 30 | 100 | | |
| | | | | በ “Basic Sciences Research” የምርምር ትኩረት አቅጣጫ ስር ምርምሮችን ማካሄድ፣ | 2.0 % | ቁጥር | 11 | 20 | 20 | 20 | 100 | 20 | 20 | 100 | | |

| | | | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | መከታተልና መደገፍ | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | 18. 0% | | | | | | | | | | | |
| | የምርመር ቴኮኖሎጂ ሽግግር እና ህትመትን ማሳደግ | የተሻሻለ የቴክኖሎጂ ሽግግርና የህትመት ስራ | የተሻሻለ የቴክኖሎጂ ሽግግርና ስራ | በአርሶ አደር ማሰልጠኛ ማእከላት አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን በሰርቶ ማሳያ መስራትና መምረጥ | 4.0 % | የማእከ ላት ቁጥር | 40 | 50 | 50 | 50 | 100 | 50 | 50 | 100 | | |
| | | | | የተሻሻሉ ቴክኖሎጂዎችን (የሰብልና የመኖ ዝርያዎች፤ የእንስሳት፤ የንብ፤ የውሃ ቆጣቢ ቴክኖሎጂ፤ የምግብ ድንች ማከማቻ፤ የተንቀሳቃሽ የዶሮ ቤት) በሰርቶ ማሳያ ማስተዋወቅ፤ | 3.0 % | የቴክኖ ሎጂ ብዛት | 25 | 30 | 5 | 6 | 120 | 30 | 41 | 137 | | |
| | | | | የተሻሻሉ ቴክኖሎጂዎችን በዩኒቨርስቲው ማዕከላት፤ በኩታ ገጠም አርሶ አደር ማሳዎችና በዘር አምራች ማህበራት ጋር በመተባበር ማባዛት፤ | 4.0 % | በኩንታ ል | 1000 | 4500 | 800 | 2053 | 257 | 4500 | 6258. 7 | 139 | - | የአመ ቱ እቅድ በስህ ተት 1500 ተብ ሎ የተጻ ፈው ወደ 4500 ተቀይ ሯል፡ ፡ |
| | | | | ስለቴክኖሎጂ አጠቃቀም ለባለድርሻ አካላት (ለአርሶ አደር፤ ለግብርና ልማት ሰራተኛ፤ | 1.0 % | የሰልጣ ኝ ቁጥር | 220 | 300 | - | 189 | - | 300 | 341 | 114 | - | |

| | | | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | ለጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች) ስልጠና መስጠት፣ | | | | | | | | | | | | |
| | | | | ለባለድርሻ አካላት የመስክ ቀን ማዘጋጀት፣ | 1.0 % | የመስክ ቀን ብዛት | 1 | 3 | - | 1 | - | 3 | 8 | 267 | | |
| | | | | የምርምር አውደ ጥናቶችን ማካሄድ (አመታዊ እና ሌሎች የምርምር አውደ ጥናትናቶች)፣ | 2.0 % | የአውደ ጥናት ብዛት | 5 | 4 | - | 1 | - | 4 | 6 | 150 | | |
| | | | | የምርምር አግዚቢሽን ማዘጋጀት፣ | 1.0 % | የኤግዚ ቢሽን ቁጥር | 4 | 4 | 1 | 3 | 300 | 4 | 7 | 175 | | |
| | | | | የተደራጁ ወጣቶችን የቴክኖሎጂ ተጠቃሚ ማድረግ | 1.0 % | የማበራ ት ቁጥር | 0 | 3 | - | - | - | 3 | 5 | 166.7 | | |
| | | | | የሴቶችን በቴክኖሎጂ (ሀይል ቆጣቢ ምድጃ፣ ዘመናዊ ዶር እርባታ) ተጠቃሚነታቸውን ማጎልበት | 2.0 % | በማህበ ራ ብዛት | 1 | 1 | - | - | - | 4 | 3 | 75 | | |
| | | | የህትመት ስራ | የምርምር ህትመቶችን ማሳተም (አምስት ጆርናሎች፣ አራት ፕሮሲዲንግ፣ መመሪያ ሰነዶች እና መጽሄት) | 3.0 % | የህትመ ት አይነት ብዛት | 9 | 18 | 1 | 5 | 500 | 18 | 18 | 100 | | |
| | | | | የተለያዩ ሳይንሳዊ የምርምር መጣጥፎችን (articles) በሚገመገሙ (Peer-reviewed) | 1.0 % | የመጣ ጥፎች ብዛት | 10 | 15 | - | 6 | - | 15 | 16 | 107 | | |

| | | | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | ጆርናሎች እንዲታተሙ የገንዘብ ድጋፍ ማድረግ | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | 23.0 % | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | 12% | 14 | | | | | | | | | | |
| የፋይናንስ / የበጀት እይታ | የምርመር ድጋፍ ምንጮችን ማሳደግ | ያደገ የምርመር ድጋፍ ምንጮች | የምርምር ድጋፍ እንዲሰጡ ፕሮፓዛሎችን መጻፍ | ከኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት ጋር እና ሌሎች በሀገር ውስጥ ካሉ ድርጅቶች ጋር በመተባበር የምርምር ድጋፍ ማግኘት | 3.0 % | ብር በሚሊየን | 1.2 | 1.2 | 0.35 | 0.35 | 100 | 1.2 | 1.2 | 100 | | |
| | | | | በውጭ ሀገር ካሉ የምርምር አካላት ጋር በመተባበር የምርምር ድጋፍ ማግኘት | 3.0 % | ብር በሚሊዮን | 10 | 12 | 3 | 4 | 133 | 12 | 15 | 125 | | |
| | | | | | 6.0 % | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | | | |
| | የሐብት አጠቃቀም ስልጠትን ማሻሻል | የተሳለጠ የሀብት አጠቃቀም | የግብዓቶችን አጠቃቀም ማሻሻል | በከፍተኛ ወጪ ከሌሎች ቦታዎች የሚመጣውን የእንስሳት መኖ በአካባባው በማምረት ወጭን መቀነስ | 1.0 % | % | - | 75 | 25 | 25 | 100 | 100 | 100 | 100 | | |
| | | | | የበጀት አጠቃቀምን ማሻሻል | 1.0 % | % | 100 | 100 | 25 | 25 | 100 | 100 | 100 | 100 | | |
| | | | | የምርምር ፈንዶችን በአግባቡ ጥቅም ላይ መዋላቸውን መከታተል | 1.0 % | የግምገማ ቁጥር | 2 | 4 | 1 | 1 | 100 | 4 | 4 | 100 | | |
| | | | | የመስከ ጉብኝትና ክትትል ማድረግ | 1.0 % | ቁጥር | | 4 | 1 | 1 | 100 | 4 | 4 | 100 | | |
| | | | | የምርምር ቴክኖሎጂዎችና | 1.0 % | ብር በሚሊ | 4 | 6 | - | 0.9 14 | - | 6 | 5.71 4 | 95 | | |

| | | | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | ተረፈ ምርቶችን የገቢ ምንጭ እንዲሆኑ ማስቻል | | የን | | | | | | | | | | |
| | | | | አገልግሎት የማይሰጡ ንብረቶችን ስራ ላይ እነዲውሉ ማስቻል | 1.0 % | % | | 75 | - | - | - | 75 | 75 | 100 | | |
| | | | | | 6% | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | | | |
| የዉስጥ አሰራር ሂደት ዕይታ | | | | | 10% | 28 | | | | | | | | | | |
| | የስራ ሂደቶችን ቅልጥፍናና ስልጠት ማሳደግ | ያደገ እና የተሳለጠ የስራ ሂደቶች | የስራ ሂደቶች ቀሎጣፋ ፣ ግልጽ እና ለየተጠቃሚው ምቹ ማድረግ | አቅም መገንባት፣ ክትትል ማድረግ | 4% | የመድረክ ቁጥር | 4 | 4 | 1 | 1 | 100 | 4 | 4 | 100 | | |
| | | | | መልካም አስተዳደርን ለማስፈን የልማት ሰራዊት መገንባት፡ መከታተልና መደገፍ | 3% | የልማት ሰራዊት ብዛት | 20 | 20 | 20 | 44 | 220 | 20 | 44 | 220 | | የምርምር ትኩረት መስኮች በአዲስ መልክ ስለተደራጁ |
| | | | | የመስከ ጉብኝት፣ ክትትል፣ ግምገማና ድጋፍ ማድረግ | 3% | የድጋፍ፣ ክትትል ቁጥር | | 12 | 3 | 3 | 100 | 12 | 12 | 100 | | |
| | | | | | 10% | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | | | |
| የመማማርና እድገት ዕይታ | | | | | 15% | 18 | | | | | | | | | | |
| | የአመራር ብቃትን፡የስራ አቅምንና ተነሳሽነትን | ያደገ የአመራር ብቃትና ተነሳሽነት፤ | የሰራተኛውን አቅም መገንባት፤ መሳብ፤ | የስራ ላይ ስልጠና መስጠት (on job Training) | 1.0 % | የሰልጣኝ ብዛት | 40 | 40 | 40 | 40 | 100 | 40 | 40 | 100 | | |

| | | | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ማሳደግ | | ማነቃቃት፣ መሸለም ማቆየት | የስራ አመራር እና የስራ የአፈጻጸም ሪፖርት አቀራረብ ላይ ስልጠና መስጠት | 1.0 % | የሰልጣኞች ብዛት | 19 | 22 | - | 20 | - | 22 | 20 | 91 | - | |
| | | | | በስራ ምዛና ከፍተኛ ውጤት ላመጡ ስራተኛ ሽልማት መስጠት | 1.0 % | የተሸላሚ ብዛት | 7 | 10 | 5 | 9 | 180 | 10 | 9 | 90 | - | |
| | | | | የልምድ ልውውጥ ጉብኝት ማድረግ፣ መልካም ተሞክሮን መቀመር | 1.0 % | የተሳታፊ ብዛት | 10 | 18 | 4 | 0 | 0 | 18 | 21 | 117 | | |
| | | | | ለምርምር የቴክኒክና የመስክ ረዳቶች፣ ተመራማሪዎች፣ ስልጠናን መስጠት (የንድፈ ሀሳብ አጻጻፍ፣ በመረጃ አያያዝ፣ እና ትንተና፣ የሳይንሳዊ ጽሁፍ አጻጻፍ) አጫጭር ስልጠናዎችን መስጠት | 1.0 % | የሰልጣኞች ብዛት | 388 | 570 | 315 | 138 | 43 | 570 | 215 | 51.4 | | |
| | | | | | 5.0 % | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | | | |
| | የምርምር ፋሲሊቲዎችን ማስፋፋትና ማዘመን | የተስፋፉና የዘመኑ የምርምር ፋሲሊቲዎች | የምርምር ፋሲሊቲዎች ለምርምር ምቹ እንዲሆኑ ማሰቻል | የምርምር ጣቢያዎችን የይዞታ ማረጋገጪያ ማሰራት/ማውጣት | 2.0 % | ቁትር | 3 | 4 | 1 | 6 | 600 | 4 | 8 | 200 | - | |
| | | | | በድሬዳዋ ምርምር ጣቢያ ሁለት ክፍል ቢሮ ስራን ማጠናቀቅ | 1.0 % | % | | 100 | - | - | - | 100 | 100 | 100 | | |

| | | | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | በግራዋ የምርምር ጣቢያ የውሃ ቦታዎችን መለየትና ማጎልበት | 1.0 % | % | | | - | 75 | - | 80 | 75 | 94 | | |
| | | | | በኤረር ለቆላ ፍራፍሬ እና አትክልት ምርምር የሚያገለግል አዲስ የምርምር ጣቢያ ማቋቋም | 1.0 % | ቁጥር | 0 | 1 | - | - | - | 1 | 1 | 100 | - | |
| | | | | ለምርምር ጣቢያዎች እና ስራዎችን የሚያስተዋውቅ ዘጋቢ ፊልምና/ጽሁፍ ዶኩመንተሪ ማሰራት | 1.0 % | ቁጥር | 0 | 2 | - | 2 | - | 2 | 2 | 100 | - | |
| | | | | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | 10 % | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | | | |